EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 7

## የእንስሳት ግዛት: ከሲጥ ሲጥ እስከ ማጓራት

PK3



AppleTree

# ክፍል 7


## የእንስሳት ግዛት: ከሲጥ ሲጥ እስከ ማጓራት

©2021
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከዚህ በታች በቅጂ መብት የተያዙትን መብቶች ሳይገድብ ፣ የትኛውም የዚህ ህትመት ክፍል  እንደገና ሊባዛ ፣ ሊከማች ወይም ወደ ሌላ የማስመለሻ ስርዓት ሊተላለፍ አይችልም  ፣ ወይም በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ ፣ ሜካኒካል ፣  ፎቶ ኮፒ ማድረግ ፣ መቅዳት ወይም በሌላ መንገድ) ያለ ቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ።

AppleTree Institute for Education Innovation
1801 Mississippi Ave SE, 3rd Floor
Washington, DC 20020

የቅጂ መብት © 2021 ጽሑፍ እና ስዕሎች። AppleTree Institute(አፕል ትሪ ኢንስቲትዩት) መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# PK3 ክፍል 7 ምልከታ





**ውድ ቤተሰቦች፣**

ወደ ክፍል 7 እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 7 ስር ልጅዎ ስለ እንስሳትና እንስሳት ስለሚኖሩባቸው የተለያዩ ቦታዎች ይማራል።

## ክፍል 7 መጻህፍት




- *Nolan's Safari/የኖላን ሳፋሪ* በ Felicia R. Truong
- *The Zoo/የዱር እንስሳት ማቆያ* በ Ruth Ebisuzaki
- *Tying My Shoes/ጫማዎቼን ማሰር* በ Julie Fowler
- *Count the Noisy Birds/ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር* በ Beryl Salinger Schmitt

*በተጨማሪም፣ ለሁሉም መጻህፍት ቀድመው የተቀዱ ንባቦች ለአዋቂዎች ጠቃሚ ምክሮች /Tips for Adults፣ የእንስሳት ግዛት በሚለው ስር በሚገኘው Sparkler መተግበሪያ ላይ ማግኘት ይቻላል።*

***ECR @ Home Activities: የECR @ Home Activities/ የቤት ውስጥ ተግባሮች በቴምፕሬት ደን፣ ሳቫና፣ ውሀ ውስጥ ስለሚገኙና ስለ እርሻ እንስሳት የተመለከተ ትምህርትን ይይዛሉ። ልጅዎ በተጨማሪም እስከ 5 የሚደርሱ የተለያዩ ቁሶችን ይሰራል፣ እስከ 7 የሚደርሱ ቁሶችን ይቆጥራል፣ እራስን ችሎ ስለመስራትና እራስን ስለመርዳት ክህሎቶች በተመለከተ ይናገራል እንዲሁም ጥንድ ቃላትን ይመሰርታል።***

***እነዚህን ተግባሮች ለግብይት በሚወጡበት ወይም የእግር መንገድ በሚያደርጉበት ወቅት የሚያዩዋቸውን እንስሳት በመመልከትና ለይተው በማወቅ ማስፋፋት የሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ። ስለ እንስሳቱ አፈጣጠር መነጋገር፣የእግሮቻቸውን ብዛት መቁጠር፣ እና ስለሚያዩዋቸው የተለያዩ አይነት እንስሳት ማነጻጸርና መነጋገር ይችላሉ። በተጨማሪም ከልጅዎ ጋር አልባሳት በምታጥቡበት ወቅት አንድ ላይ ሆናችሁ መቁጠርና ጥንድ ካልሲዎች ማዘጋጀት ትችላላችሁ።***

## ክፍል 7 ቃላት

- እንስሳ
- ዛጎል ድንጋይ
- የቤት እንስሳ
- በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳት
- መኖሪያ
- ነፍሳት
- የህይወት ዑደት
- ሳቫና
- የዱር እንስሳ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 1


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 7 ሳምንት 1 ምልከታ

## የቴምፕሬት ደን እንስሳት

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

ስለ ቴምፕሬት ደን እንስሳት በተመለከተ ይማራል። ልጅዎ እስከ 5 ቁሶችን ይሰራል፣ ጥንድ ቃላት መመስረትን ይለማመዳል እንዲሁም ስለ ህይወት ኡደቶች ይማራል።
እነዚህን ተግባሮች ቀኑን በሙሉ ልብስ በሚያጥቡበት ወቅት ጥንድ ካልሲዎች በማዘጋጀት ወይም ጠረጴዛ ከማዘጋጀትዎ በፊት ማንኪያዎችን በማዘጋጀት ማስፋፋትና ማቀናጀት ይችላሉ። ጥንድ ቃላትን ለመቀላቀል ወይም ለመለያየት ከልጅዎ ጋር ጌሞችን ሊጫወቱ ይችላሉ።





### ቁልፍ ቃላት




## እንስሳት

ልጆች ያሏቸው፣ ምግብ፣ ውሀና አየር የሚያስፈልጋቸው፣ ፍላጎታቸውን ማሳካት የሚችሉ እና የተለያዩ አካሎች ያሏቸው ህይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው።



## ነፍሳት

ስድስት እግሮችና አንዳንድ ጊዜም ክንፎች ያሏቸው ጥቃቅን ፍጡራን ናቸው።



## የህይወት ዑደት

እንስሳት ወይም የሰው ልጆች ወደ አዋቂነት የእድሜ ደረጃ የሚቀየሩበት ጊዜ ነው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለ እንስሳት እና እንስሳትን ምን ልዩ እንደሚያደርጋቸው በመማር ትጀምራላችሁ። መርሀ ግብሩን ከመጀመርዎ በፊት ስለ እንስሳት መማር ስለሚፈልጉት ስለሆነ ነገር ይሳሉ እንዲሁም ይጻፉ።

## ያስቡበት!



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## **STEM:** የተለያዩ የጫካ እንስሳት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ጥንድ ጥንቸሎች፣ ቀለም መቀቢያዎች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀስ**



- ልጅዎን **እስኪ በዚህ ገጽ ላይ ስንት ጥንቸሎች እንዳሉ ቁጠር** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ጥነቸሎቹን ቀለም መቀባት እና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ** ይበሉት። ልጅዎን እንደ አስፈላጊነቱ ጥንቸሎቹን ቆርጦ በማውጣት ላይ ያግዙት።
- ከዚያም በኋላ ልጅዎን ከ5 የማይበልጡ ጥንቸሎችን የሚይዙ የተለያዩ ምድቦች እንዲሰራ ይጠይቁት፤ ለምሳሌ፡ እስኪ 3 ጥንቸሎችን የሚይዝ ምድብ ስራ፣ አሁን ደግሞ 2 ጥንቸሎችን የሚይዝ ምድብ ስራ፣ ወዘተ

## በግል መማር፥ የቴምፕሬት ደን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንስሳት፣ የቴምፕሬት ደን እንስሳት፣ ከለር መቀቢያዎች**



የቴምፕሬት ጫካ እንስሳት (FE)

- ለልጅዎ **በዚህ ሳምንት በቴምፕሬት ደን ውስጥ ስለሚገኙ እንስሳት በተመለከተ ትማራለህ። የቴምፕሬት ደን እጅግ በጣም ብዙ ዛፎች የሚገኙበት ቦታ ነው። ቦታው አራት ወቅቶች ያሉት ሲሆን እነዚህም ክረምት፣ ፀደይ፣ በጋ እና መኸር ናቸው። አንዳንዶቹ ዛፎች በፀደይ ወቅት ቀለማቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ። በክረምት ወቅት ቅጠሎቻቸው ሊረግፉ የሚችሉ ቢሆንም በፀደይ ወቅት ግን መልሰው ይተካሉ** ብለው ይንገሩት።
- ስዕሎቹን በመጠቀም በቴምፕሬት ደን ውስጥ ስለሚኖሩ እንስሳት ይንገሩት።
- ለልጅዎ **የቴምፕሬት ደን ስዕል መቀባት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሉን ቀለም እንዲቀባ ወይም የራሱን ስዕል እንዲስል ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ በቴምፕሬት ደንህ ውስጥ ስለሚገኙ እንስሳት ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።
- የእንስሳት ስዕሎቹን በዚህ ወር ውስጥ በሙሉ እንዲጠቀሙባቸው ያስቀምጧቸው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## ማንበብና መጻፍ፥ የድምጽ ቀለሞችን መቀላቀል

- ለልጅዎ **የድምጽ ቀለሞች የቃል ምቶች ናቸው። እስኪ rooster የሚለውን ቃል ምቶች አንድ ላይ እናገናኝ: roos-ter** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እስኪ የድምጽ ቀለሞችን እንቀላቅል! መቀለላቀል ማለት አንድ ላይ ማድረግ ነው** ይበሉት።
- **An** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **i** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **mal። An-i-mal። የቃሉን ክፍሎች አንድ ላይ ቀላቅላቸው። የምትሰማው ቃል ምን ይሆናል?** ብለው ይጠይቁት።
- ለልጅዎ ሞቅ ያለ ሙገሳ ማድረግዎን አይርሱ! **በጣም ጥሩ ስራ ነው!**
- ሙከራውን: forest (for-est) እና safari (sa-far-i) በሚሉት ቃላት ደግማችሁ ስሩ።

## ያንብቡ፥ የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari


**እስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*የኖላን ሳፋሪ /Nolan's Safari*]

- ከልጅዎ ጋር አብረው ሆነው *የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም ከገጽ 2-5 ያሳዩት። ቀጥለውም **በመጀመሪያ ኖላን ምንም እንዳልተበሳጨ ቢናገርም መበሳጨቱ ግን ፊቱ ላይ ያስታውቅበት ነበር። ኖላን ምን አይነት ስሜት ተሰምቶት ነበር ብለህ ታስባለህ? ይህን እንዴት መናገር ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።

በተጨማሪም የዚህን መጽሀፍ በቅድሚያ የተቀዳ ንባብ ከSpakler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ክፍል፡ የእንስሳት ግዛት ከሚለው ስር ማግኘት ይችላሉ።

**የኖላን ሳፋሪ**

FELICIA R. TRUONG, EDD
ሰዐሊ RACHEL ANNE BLIER







©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።















©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።
















©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።














©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

















©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## STEM: የእንስሳት ባህሪያት




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [የእንስሳት ባህሪያት፣ እንስሳት፣](#) እንደ ማንኪያ፣ ሳህን ወይም ከለር መቀበቢያዎች የመሳሰሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች**

- ስለ እንስሳትና ባህሪያቶቻቸው ለልጅዎ ለመንገር ስዕሎቹን ይጠቀሙ። ለልጅዎ **ሁሉም እንስሳት ባህሪያት ወይም ልዩ የሚያደርጓቸው ነገሮች አሏቸው** ብለው ይንገሩት።
- **እንስሳት የሚንቀሳቀሱ፣ ምግብና ውሀ የሚያስፈልጋቸው፣ የአካል ክፍሎች ያሏቸው እና ልጆች ያሏቸው ህይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እስኪ ጌም እንጫወት። እኔ የሆነ ነገር አሳይሀለሁ። አንተ ደግሞ ያሳየሁህ ነገር እንስሳ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ትነግረኛለህ** ብለው ይንገሩት።
- የአንድ እንስሳ ስዕል ያሳዩት እና እንስሳ እንዲሆን ስላደረጉት ባህሪያት ይንገሩት፤ ምሳ፡ እባብ ይንቀሳቀሳል፣ ይመገባል እንዲሁም ልጆች አሉት? ብለው መጠየቅ። ይህን ከማይንቀሳቀስ እና ህይወት ከሌለው የቤት ውስጥ ቁስ ጋር ያነጻጽሩ።
- ስዕሎቹን ለዚህ ክፍል በሙሉ ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፡ ነፍሳት ቀለም መቀባት

***አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ወረቀት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል፣** በአማራጭነት - የማስዋቢያ ቁሶች ለምሳሌ የአይን መቀቢያዎች፣ የቱቦ ማጽጃዎች ወይም ለእግሮች የተሰባበረ ፓስታ፣ ወዘተ*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው የነፍሳት ስዕሎችን ከስልክዎ ወይም ታብሌት ላይ ተመልከቱ። ለልጅዎ ስለተወሱ የነፍሳት ባህሪያት ይንገሩት። ነፍሳት 6 እግሮች፣ አንቴና እእ ሶስት የአካል ክፍሎች (ራስ፣ እምቢያ/ ክርክር አንገትና ሆድ) አላቸው።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ መሳልና መቀባት የሚፈልገውን ነፍሳት (እውነተኛ ወይም ሰው ሰራሽ) እንዲመርጥ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ነፍሰትህ ንገረኝ። እስኪ እግሮቹን በጋራ እንቁጠራቸው** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ




## ማንበብና መጻፍ፡ ጥንድ ቃላት

- ለልጅዎ **እስኪ ስዕሎች ሳንጠቀም ጥንድ ቃላትን እንመስርት!** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ ሁለት ቃላት እናገራለሁ። አንተ ደግሞ አንድ ጥንድ ቃል ለመፍጠር ቃላቱን አንድ ላይ ታገናኛለህ** ይበሉት።
- **ሁለቱ ቃላት እነዚህ ናቸው: "bed"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **"time"። ሁለቱን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸዋለሁ ማለትም bed** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **time፣ bedtime** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግሞ የአንተ ተራ ነው። እስኪ እነዚህን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸው: "foot"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **"ball"፣ foot** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **ball።** ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገውም ገና በመማር ላይ ስለሆነ ምንም አይደለም። ልጅዎን ለሙከራው ያሞግሱት እና ቃላቱን ደግመው ይናገሯቸ ። ከዚያም ጥንድ ቃሉን መልሰው ይናገሩ። **በጥንቃቄ አስብ! አንድ ላይ football የሚለውን ቃል ለመስራት Foot** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **ball።**
- ሙከራውን basketball እና flashlight በሚሉት ቃላት ደግመው ይስሩ።

## የጆርናል ሙከራ፡ ሳፋሪ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ ከለር መቀቢያዎች፣ እርሳስ፣ የሳፋሪ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለ *የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari* ይነጋገሩና ልጅዎን በሳፋሪ ቢጓዝ ምን አይነት ስሜት ሊሰማው እንደሚችል ይጠይቁት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስሜቱን እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- ቀጥለውም **እስኪ በሳፋሪ ላይ ብትጓዝ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማህ ንገረኝ። መጀመሪያ ላይ ልክ እንደ ኖላን ትበሳጫለህ?** ብለው ይጠይቁት።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




እንስሳት ምግብ ይመገባሉ



እንስሳት ልጆች ይወልዳሉ



እንስሳት ይንቀሳቀሳሉ




እንስሳት የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች አሏቸው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ ኖላን ወደ ሳፋሪ ለመሄድ ፈርቶ ነበር። አንተ ብትሆን ምን ይሰማሃል?


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## **STEM:** ምን ያክል ጣቶች አሉ?

- 5ቱን ጣቶችዎን ወደ ላይ ያድርጉ እና ልጅዎን **ስንት ጣቶች አሉኝ?** ብለው ይጠይቁት። ለልጅዎ ጣቶችዎን እንዲቆጥራቸው ይፍቀዱለት። ከዚያም ልጅዎን በተመሳሳይ የእጁን ጣቶች ወደ ላይ እንዲያነሳ ያድርጉት።
- በ0 (ጡጫዎን ያሳዩት) እና 7 መካከል ከ3-4 ያክል ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎን ለጥረቶቹ ያሞግሱት። **ጥሩ ሰርተሀል፣ በታታሪነት ነው የሰራኸው!**
- ለልጅዎ ለመቁጠር ጣቶቹን መጠቀም በኋላ ላይ ለሂሳብ ስሌትና የችግር አፈታት ይረዳዋል።

## በግል መማር፥ እችላለሁ!

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለር መቀቢያዎች**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ልጅዎ በራሱ ማድረግ ስለሚችላቸው ስለተለያዩ ነገሮች ተነጋገሩ፤ ምሳ፡ ካልሲዎቹን መልበስ፣ ቀለም መቀባት፣ ወዘተ
- ለልጅዎ **በራስህ ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ዝርዝር ማዘጋጀት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን በራሱ ማድረግ የሚችላቸውን ነገሮች እንዲስልና እንዲጽፍ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ በዝርዝርህ ላይ ስላሰፈርካቸው ነገሮች ንገረኝ። ዋው፡ እነዚህ በጣም ብዙ ነገሮች ናቸው፤ ሁሉንም ነገሮች በራስህ ማድረግ ትችላለህ!** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎ በ‹‹እችላለሁ›› ዝርዝሩ ላይ ሊጨምር እና ማድረግ የሚችላቸውን ሁሉንም ነገሮች ለማስታወስ እንዲረዱት ዝርዝሩን የተለየ ቦታ ሊለጥፍ ይችላል። ዝርዝሩን በቀን 12 ለሚሰሩ ተግባሮች ያስቀምጡት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## ማንበብና መጻፍ፥ ስሜትን በስም መግለጽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [ስሜቶች]**




- ለልጅዎ **ሰውነታችንና ፊታችን ምን አይነት ስሜት እየተሰማን እንደሆነ በተመለከተ ብዙ ነገሮችን ይናገራሉ። እስኪ ስሜትን በስም የመግለጽ ጨዋታ እንጫወት። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ልትነግረኝ ትችላለህ።**
- ከሚከተሉት መከካከል 2-3 ስሜቶችን ወይም በልጅዎ የሚገለጹ የተለመዱ ስሜቶችን በመጠቀም ጌም ተጫወቱ:
  - ንዴት
  - ሀዘን
  - ደስታ
  - መገረም
  - መበሳጨት
- እንደ አስፈላጊነቱ ስዕሎቹን በመጠቆም ከልጅዎ ጋር እነዚህ ስሜቶች መቼ ተሰምተውት እንደነበር በተመለከተ ይነጋገሩ።

## ያንብቡ፥ የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari

**የኖላን ሳፋሪ**

FELICIA R. TRUONG, EDD
ሰዐሊ RACHEL ANNE BLIER

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [*የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari*]**




- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari* ምንባብን ያንብቡ።
- በሚያነቡበት ወቅት ልጅዎ አንድ ላይ የሚያያቸውን እንስሳት እንዲቆጥር ያድርጉ።
- ዚያም **ኖላን 5 የኬፕ ጎሾች** (የአንድ እጅዎን 5 ጣቶች ወደ ላይ ያንሱ) **እና 1 ነብር** (የአንድ እጅዎን 1 ጣት ወደ ላይ ያንሱ) **አይቷል። የበለጠ ቁጥር ያላቸው የኬፕ ጎሾች ወይስ ነብሮች ነበሩ?** ብለው ይጠይቁት።
- **አዎ፤ ጎሾች! ኖላን ከነበሮቹ ይልቅ በቁጥር የበዙ ጎሾች አይቷል።**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 1 ቀን 3

## እስኪ እንንቀሳቀስ: እንስሳትን ማስመሰል


- ለልጅዎ **እስኪ ጌም እየተጫወትን የተለያዩ እንስሳትን ለማስመሰል እንሞክር። አንዳችን ሌላኛችን የትኛውን እንስሳ ለማስመሰል እየሞከርን እንደሆነ እንገምታለን** ብለው ይንገሩት።
- የተለያዩ እንስሳትን አስመስለው ለመንቀሳቀስ ተራዎን ይውሰዱ፤ ምሳሌ፡ ልክ እንደ ካንጋሮ መዝለል፣ እንደ አንበሳ ማጓራትና ጋማ ማወዛወዝ፣ ወይም እንደ ወፍ ክንፎች ማርገፍገፍ።
- ተግባሩን የበለጠ ፈታኝ ለማድረግ ልዩ ምድብ ያላቸው እንስሳትን አስመስለው ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፤ ምሳ፡ በአፍሪካ ሳፋሪ ውስጥ የምታዩዋቸው እንስሳት፣ የውሀ ውስጥ እንስሳት፣ በራሪ እንስሳት፣ ወዘተ

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ እንስሳችን


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ከለር መቀቢያዎች እና/ወይም ቀለም፣ እርሳሶች**

- ለልጅዎ **እስኪ በጋራ ሆነን ስለ አንድ እንስሳ እንማር። የበለጠ መማር የሚኖርብን ስለ የትኛው እንስሳ ነው?** ብለው ይጠይቁት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለዚህ እንስሳ በተመለከተ በትንሹ ተጨማሪ ነገሮችን ለማወቅ ስልክ፣ ታብሌት ወይም መጽሀፍ ይጠቀሙ፤ ለምሳሌ፡ የት እንደሚኖሩ፣ ምን እንደሚመገብ፣ ወዘተ
- ከዚያም በጋራ ሆናችሁ ስለዛ እንስሳ የተማራችሁትን ነገር በስዕል አስቀምጡ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ደስተኛ



ሃዘን



ንዴት



የተረበሸ



የተረጋጋ



ኩራት



ያዘን



እንቅልፍ መጫጫን



በጣም መደሰት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## STEM: የህይወት ዑደት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የህይወት ዑደት፣ ከለር መቀቢያዎች**



- ለልጅዎ **የህይወት ዑደት የአንድ እንስሳ ወይም ሰው ወደ አዋቂነት እድሜ መቀየርን ያመለክታል** ብለው ይንገሩት።
- **እስኪ የቢራቢሮ እና የሰው ልጅ ሁለት የህይወት ኡደቶችን እንመልከት።** ስለ ቢራቢሮ የህይወት ዑደት ለማብራራት ስዕሉን ይጠቀሙ፡ ከእንቁላልነት ወደ አባጨጓሬነት፣ ከዚያም ወደ ክሪሴይልስ (አባጨጓሬው ቢራቢሮ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት በጠንካ ቀፎ የሚሸፈንበት ደረጃ)።
- ከዚያም ስለ ሰው ልጅ የህይወት ዑደት ይንገሩት፤ ከጨቅላ ህጻንነት ወደ ህጻንነት፤ ቀጥሎ ወደ ጉርምሳና ከዚያም ወደ አዋቂነት
- ከዚያም ለልጅዎ ስዕሎቹን ቀለም እንዲቀባ ይፍቀዱለት።

## በግል መማር፥ የራሴን እንስሳ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ውህማ ቀለም ጥቅል ወይም ከለር መቀቢያዎች፣ *በአማራጭነት - እንደ የአይን መቀቢያዎች፣ የተሰባበረ ፓስታ፣ ጥጥ፣ ማጣበቂያ፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች የመሳሰሉ የቤት ውስጥ የእንስሳ ማስዋቢያ ቁሳቁሶች።***


- ለልጅዎ **እስከ አሁን ስለ ብዙ የተለያዩ አይነት እንስሳት ተምረናል። አሁን የራስህን እንስሳ መፍጠርና ቀለም መቀባት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የራሱን እንስሳ እንዲፈጥርና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ።
- ከዚያም ልጅዎን ስለፈጠረው እንስሳ እንዲያብራራ ይፍቀዱለት - ስሙን፣ የሚኖርበትን ቦታ፣ የሚመገበውን ምግብ፣ ወዘተ


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ




## ማንበብና መጻፍ፥ እስኪ ስለ ስዕሉ ንገረኝ




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *[የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari]*

- ለልጅዎ *የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari*ን ገጽ 16-17 ያሳዩት።
- ከዚያም **ምን እየከሰተ ከሆነ ነው?** ብለው ይጠይቁ።
- ልጅዎ ተጨማሪ ዝርዝሮችን እንዲያክል ለማድረግ የክትትል ጥያቄዎችን ሊጠይቁት ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡ **ኖላን በባይናኩላሩ ምን ለማየት እየሞከረ ነው ብለህ ታስባለህ? ኖላን ከነርሱ በተሻለ ማየት ይችላል ብለህ ታስባለህ? ነብሩ ያለው የት ነው?**
- ከዚያም **ባይናኩላር በርቀት ያሉ ነገሮችን አቅርቦ ለማየት ይረዳናል** ብለው ያብራሩለት።


## የጆርናል ሙከራ፥ የደን እንስሳት





**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር መቀቢያዎች፣ የደን እንስሳት የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ስለተለያዩ የጫካ እንስሳት ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ለማየት ስሊፈልጋቸው እንስሳት እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ማየት ስለምትፈልጋቸው የጫካ እንስሳት በተመለከተ ንገረኝ። ይህን እንስሳ ለምን መረጥከው?**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

ማየት ስለሚፈልጉት የደን እንስሳ ጻፉ እና ስዕል ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 1 ቀን 5

## STEM: ምን ያክል ቁሶች አሉ?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንደ ቀለም መቀቢያዎች ወይም ማንኪያዎች የማሰሉ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፣ የእያንዳንዳቸው ብዛት 7**

- ለልጅዎ 7 የከለር መቀቢያዎች ያሳዩት እና **ምን ያክል የከለር መቀቢያዎች አሉ?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ እያንዳንዱን ከለር በሚያሳዩበት ወቅት አንድ ላየ ሆናችሁ ቁጠሩ።
- ሙከራውን በ0 እና 7 መካከል ባሉ መጠኖች ላይ ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ። ልጅዎን ቁስዎን ጠቁሞ እንዲያሳይዎት እና ቁሶቹን እንዲቆጥሩ እንዲጠይቅዎት ይፍቀዱለት።
- ስራውን የበለጠ ፈታኝ ለማድረግ ልጅዎን በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ ከ0-7 ቁሶቹን እንዲያመጣልዎ ይጠይቁት። ይህ ለልጅዎ ከባድ ከሆነ አንድ ላይ ሆናችሁ ስሩ!

## በግል መማር፥ የደን እንስሳት ትእይንት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የመጫወቻ ሊጥ ወይም [Pl በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ፣ ](#) [ለእንስሳት](#)፣ *በአማራጭነት - ቅጠሎች፣ ቀጫጭን ዱላዎች ወይም የአሻንጉሊት እንስሳት***

- ለልጅዎ በደን ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ እንስሳትን ያሳዩት እና በደን ውስጥ በተጨማሪ ምን ሊያይ እንደሚችል ያወያዩት።
- ለልጅዎ **ከመጫወቻ ሊጥ እንስሳት ልትሰራ እና የሚኖሩበትን ደን በቀጫጭን ዱላዎች እና ሌሎች ከቤት ውጭ ወይም በቤት ውስጥ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ልትሰራ ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ የራሱን ደን እንዲሰራ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ደንህ ንገረኝ። ወደ ሳፋሪ ብሄድ ምን አይነት እንስሳትን ላይ እችላለሁ?** ብለው ይጠይቁ።

የቴምፕሬት ጫካ እንስሳት (FE)



የቴምፕሬት የዱር እንስሳት (FE)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## ማንበብና መጻፍ፥ ዋና ገጸ ባህሪ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari***

- ለልጅዎ *የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari*ን ያሳዩት። **ቀደም ብለን *የኖላን ሳፋሪን* አንብበናል። የዚህ መጽሀፍ ዋና ገጸ ባህሪ ማን ነው? የመጽሀፍ ገፀ ባህሪያት ሰዎች ወይም እንስሳት ናቸው። ዋና ገጸ ባህሪ ማለት ታሪኩ በአብዛኛው ዬመለከተው ሰው/እንስሳ ነው።** ለልጅዎ እርዳታ ቢያደርጉለትም ምንም ማለት አይደለም። ገና እየተማረ ስለሆነ!
- **አዎ፤ ታሪኩ ስለ ኖላን በተመለከተ ነው። እንደ ወላጆቹ ያሉ ሌሎች ገጸ ባህሪያት ያሉ ቢሆንም በአብዛኛው ታሪኩ ኖላንን የተመለከተ ነው** ብለው ይንገሩት።
- **እስኪ ስለ ኖላን እንግለጽ። ስለ ኖላን ምን ታውቃለህ?** ብለው ይጠይቁት። ለልጅዎ ለማስታወስ ፈጣን የስዕል መልሶ ምልከታ ያድርጉ። አንዳንድ ምሳሌዎች ይስጡት፤ ለምሳሌ፡ **ኖላን በመጀመሪያ የተበሳጨ ይመስል ነበር ሆኖም እንስሳቱን ሲመለከተ የበለጠ ተደስቷል።** ልጅዎ ኖላን ምን እንደሚመስል፣ ምን እንደሚያደርግ እና ምን እንደሚሰማው ሊገልጽ ይችላል።




## ያንብቡ፥ የኖላን ሳፋሪ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari***

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari* ምንባብን ያንብቡ።
- ከዚያም **በታሪኩ ውስጥ ስለተፈጠሩ ነገሮች ልትነግረኝ ትችላለህ? በመጀመሪያ ምን ተከሰተ? ቀጥሎስ ምን ተከሰተ?**
- ታሪክ መልሶ መንገር ለልጅዎ ታሪክ የማስታወስና መልሶ የመናገር ክህሎቶችን እንዲያዳብር ለመርዳት አስፈላጊ ነው።

**የኖላን ሳፋሪ**

FELICIA R. TRUONG, EDD
ስዐሊ RACHEL ANNE BLIER





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሳምንት 2


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ምልከታ

## የሳቫና እንስሳት

### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥



እስከ 5 ቁሶችን ይሰራል፣ ጥንድ ቃላትን መመስረትን ይለማመዳል፣ ስለ እንስሳት አካል ክፍሎችና የቆዳ ፓተርኖች ይማራል፣ እንዲሁም በአፍሪካ ሳቫና እና በቴምፕሬት ደኖች የሚገኙ እንስሳትን ለይቶ ያውቃል።
በቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ ሆናችሁ የተለያዩ እንስሳትን በምትመለከቱበት እና የት እንደምትኖሩ በምትነጋገሩበት ወቅት - መኖሪያ ቦታችሁ የበለጠ 4 ወቅቶች ካሉት የቴምፕሬት ደን ጋር ይመሳሰላል ወይም አመቱን በሙሉ ሞቃት ከሆነው የሳቫና ሳር አብቃይ መሬት ጋር የበለጠ ይመሳሰላል? በመኖሪያ መንደራችሁ ውስጥ ምን አይነት እንስሳት ይኖራሉ?



### ቁልፍ ቃላት



## በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳት

በአለም ላይ በቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት ብቻ የቀሩ እንስሳት ናቸው።



## ሳቫና

በአፍሪካ የሚገኝ ሰፊ ከጥ ያለ ሜዳማ ሳር አብቃይ መሬት ነው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት በአፍሪካ ሳቫና ስለሚገኙ እንስሳት ትማራላችሁ፤ ለምሳሌ፡ አንበሶች፣ ዝሆኖች እና ቀጭኔዎች። መርሀግብሩን ከመጀመራችሁ በፊት በሳቫና ማየት ስለሚፈልጉት እንስሳት ይሳሉ እንዲሁም ይጻፉ።

ያስቡበት!



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 6

## STEM: ስንት እንደሆኑ አሳየኝ


- ልጅዎን **እስኪ 6 ጣቶች አሳየኝ** ይበሉት። ልጅዎ እርዳታ የሚያስፈልገው ከሆነ ጣቶቹን አንድ በአንድ እንዲቆጥር ይርዱት። ከዚያም በእጆችዎ ላይ ስንት ጣቶች እንዳሉ ያሳዩት።
- ሙከራውን ከ0 እስከ 7 ባሉት መጠኖች መካከል ከ3-4 ተጨማሪ ጊዜያት ደግማችሁ ስሩ።
- ለመቁጠር ጣቶችን መጠቀም መቻል ለልጅዎ በኋላ ላይ ለሂሳብ ስሌቶችና የችግር አፈታት ይረዳዋል።




## በግል መማር፥ የሳቫና እንስሳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንስሳት, የሳቫና እንስሳት, ከለር መቀቢያዎች**

- ለልጅዎ **በዚህ ሳምንት ስለ ሳቫና እንስሳት ትማራለህ። ባለፈው ሳምንት ባነበብነው መጽሀፍ ውስጥ ኖላን ወደ አፍሪካ ሳቫና የአደን ጉዞ ያደርጋል። ሳቫና በአፍሪካ የሚገኝ እጅግ ሰፊ ለጥ ያለ ሜዳ ሳር አብቃይ መሬት ነው** ብለው ይንገሩት።
- **ኖላን ካያቸው እንስሳት ውስጥ ጥቂቶቹን ልታስታውስ ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት። ስዕሎቹን በመጠቀም በሳቫና ውስጥ ስለሚኖሩ እንስሳት በተመለከተ ይንገሩት።
- ልጅዎን **የሳቫና ስዕል ቀለም መቀባት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሉን ቀለም እንዲቀባ ወይም የራሱን ስዕል እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ በሳቫናህ ውስጥ ስለሚገኙ እንስሳት ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።




የሳቫና እንስሳት (FE)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 6

## ማንበብና መጻፍ፥ እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት

- ለልጅዎ **እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት** ብለው ይንገሩት
- **እኔ ሁለት ቃላትን እነግርህና አንተ ደግሞ አንድ ጥንድ ቃል ለመመስረት ቃላቱን አንድ ላይ ታገናኛቸዋለህ** ይበሉት።
- **ሁለቱ ቃላት እነዚህ ናቸው: "tooth"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **"brush"። ሁለቱን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸዋለሁ ማለትም tooth** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **brush፣ toothbrush** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግሞ የአንተ ተራ ነው። እስኪ እነዚህን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸው: "wheel"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **"chair"፣ wheel** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **chair።** ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገውም ገና በመማር ላይ ስለሆነ ምንም አይደለም። ልጅዎን ለሙከራው ያሞግሱት እና ቃላቱን ደግመው ይናገሯቸው ። ከዚያም ጥንድ ቃሉን መልሰው ይናገሩ። **በጥንቃቄ አስብ! አንድ ላይ wheelchair የሚለውን ቃል ለመስራት Wheel** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **chair።**
- ሙከራውን airplane እና starfish በሚሉት ቃላት ደግመው ይስሩ።

## ያንብቡ፥ ***The Zoo/****የዱር አራዊት ማቆያ*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [***የዱር አራዊት ማቆያ***]

- ከማንበባችሁ በፊት ለልጅዎ **ይህ መጽሀፍ ስለ እንስሳት እና ወደ የዱር እንስሳት ማቆያ ጉብኝት ለማድረግ እንዴት እቅድ ማዘጋጀት እንዳለብን በተመለከተ በጣም ብዙ መረጃ የሚሰጠን በመሆኑ ምክንያት መሳጭ መጽሀፍ ነው** ብለው ይንገሩት።
- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የዱር አራዊት ማቆያ/The Zoo* ምንባብን ያንብቡ። በምታነቡበት ወቅት በገጽ 3 ላይ የሚገኘውን ካርታ ጠቁመው ያሳዩት እና **ካርታው እያንዳንዱን እንስሳ ለማግኘት ወደ የትኛው ቦታ መሄድ እንዳለብን ይነግረናል። የሜዳ አህያውን ጠቁመህ ማሳየት ትችላለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- **በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙት እንስሳት በዱር አራዊት ማቆያ ውስጥ የሚኖሩ ቢሆኑም እንስሳቱ በተጨማሪም በሳቫና ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ** ይበሉት።
- ቀጥለውም **በዱር እንስሳት ማቆያ ውስጥ የትኛውን እንስሳ ማየት ትፈልጋለህ?** ብለው ይጠይቁት።

በተጨማሪም የዚህን መጽሀፍ በቅድሚያ የተቀዳ ንባብ ከSpakler መተግበሪያ ላይ “ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች” ክፍል: የእንስሳት ግዛት ከሚለው ስር ማግኘት ይችላሉ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 7

## STEM: የእንስሳት የአካል ክፍሎች



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** **[የእንስሳት የኣል ክፍሎች ማዛመጃ]**

- ከልጅዎ ጋር የእንስሳት የአካል ክፍሎች እንዴት ጠቃሚ እንደሆኑ ለመነጋገር የስዕል ካርዶቹን ይጠቀሙ። ከዚያም **እንስሳት በተፈጥሮ እንዲረዷቸው የተለያዩ ልዩ የአካል ክፍሎቻቸውን ይጠቀማሉ። የዝሆን ኩንቢ ምግብና ውሀ ለመውሰድ ያገለግለዋል። የጉንዳን አዳኝ ረጅም አፍንጫና ምላስ ጉንዳኖችን ከጎጆቸው ውስጥ ዝቆ ለማውጣት ይረዳዋል። የዝንጀሮ ጭራ ከዛፍ ዛፍ ዘሎ እንዲንጠላጠል ይረዳዋል** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እንስሳትን ከልዩ የአካል ክፍሎቻቸው ጋር ለማዛመድ እንዲሞክር ይፍቀዱለት። ልጅዎን እንደ አስፈላጊነቱ እየረዱት ሞቅ ያለ ሙገሳ ይስጡት።
- ልጅዎ እየሰራ ባለበት ወቅት እንስሳት እንዴት ልዩ የአካል ክፍሎቻቸውን እንደሚጠቀሙ ይጠይቁት።

## በግል መማር፥ በጫወቻ ሊጥ የተሰሩ እንስሳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የጫወቻ ሊጥ ወይም [በመጫወቻ ሊጥ የተዘጋጀ ምግብ]**,

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው ልጅዎ ስሊወዳቸው የተለያዩ አይነት እንስሳት በተመለከተ ተነጋገሩ።
- ለልጅዎ **የምትወዳቸውን እንስሳት ወይም አንድ እንስሳ የመጫወቻ ሊጥ በመጠቀም መስራት ትችላለህ!** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ስለሰራኸው እንስሳ ንገረኝ። እንስሳቱ የሚኖሩት የት ነው? እንስሳቱ ለተለያዩ ነገሮች የሚረዷቸው ልዩ የአካል ክፍሎች አሏቸው?** ብለው ይጠይቁት።



በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 7

## ማንበብና መጻፍ፥ እስኪ ስለዚህ ንገረኝ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*የኖላን ሳፋሪ/Nolan's Safari*]

- ለልጅዎ *የኖላን ሳፋሪ/ Nolan's Safari.* መጽሀፍን ገጽ 6-7 ያሳዩት።
- ከዚያም **በእነዚህ ስዕሎች ላይ ምን እየተከሰተ እንደሆነ ይታይሀል?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ተጨማሪ ዝርዝሮችን እንዲሰጥ ለማበረታታት የክትትል ጥያቄዎችን ሊጠይቁት ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡ **ኖላንና እናቱ ምን አይነት ስሜት የሰማቸዋል ብለህ ታስባለህ? ይህን እንዴት መናገር ትችላለህ?**




በመጀመሪያ 2 አውራሪስ እናያለን።
ትልልቅ ቀንዶች አላቸው። እኔ በጣም፣
በእጅጉ፣ ሙሉ ለሙሉ፣ ያለምንም መዋሸት
አልፈራሁም!

## የጆርናል ሙከራ፥ እኔ ጀግና ነን

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር መቀቢያዎች፣ እርሳስ፣ የእኔ ጀግና ነኝ የጆርናል ገጽ**

- **ጀግና ማለት ፍላጎታችን ባይሆንም እንኳ እጅግ ከባድ ወይም አስፈሪ ነገር ማድረግ ነው።** ከልጅዎ ጋር የፈራ ቢሆንም እንኳን ጀግና ስለሆነበት ጊዜ ይነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ጀግና ስለሆነበት ጊዜ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ጽሁፍህ ንገረኝ። እስኪ ጀግና ስለሆንክበት ጊዜ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።



ስም፥ ____________________

ጀግና ሆናችሁ ስለምታውቁበት ጊዜ ጽሁፍ ጻፉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።










©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።









©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨውን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይክተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ጀግና ሆናችሁ ስለምታውቁበት ጊዜ ጽሁፍ ጻፉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## STEM: 5 ስጠኝ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ እንደ ከለሮች ወይም ማንኪያዎች ያሉ ቁሳቁሶች፣ እያንዳንዱ 5**



- ልጅዎን **እስኪ 5 ከለር መቀቢያዎች ስጠኝ** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ እርዳታ ካስፈለገው እያንዳንዱን ከለር መቀቢያ ጠቁሞ ያሳይ እየቆጠሩ ይንገሩት።
- ሙከራውን በ0 እና 5 መካከል ባሉ መጠኖች ከ2-3 ተጨማሪ ጊዜያት ደግችሁ ስሩ። ልጅዎን እርስዎን ከለር መቀቢያዎች እንዲሰጡት እንዲጠይቅዎ ይፍቀዱለት።
- ይህን ተግባር የበለጠ ከባድ ለማድረግ ልጅዎን በቤት ውስጥ ከሚገኙ ነገሮች መካከል ከ0 እስከ 5 ቁሶች እንዲያመጣልዎ ይጠይቁት። ይህ ከባድ ከሆነበት አንድ ላይ ሆናችሁ ስሩ!

## በግል መማር፡ የእንስሳት ፓተርን ማዛመድ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡ [የእንስሳት ፓተርን ማዛመድ](), *በአማራጭነት - ወረቀት፣ ከለር መቀቢያዎች***



- የእንስሳት ስዕሎችን በመጠቀም ከልጅዎ ጋር እንስሳት ስላሏቸው የተለያዩ ፓተርኖች በተመለከተ ይነጋገሩ። ከዚያም **እንስሳት በአካሎቻቸው ላይ የተለያዩ ፓተርኖች አሏቸው። ከእነዚህ ፓተርኖች መካከል አንዳንዶቹ ጠላቶቻቸው እንዳያዩዋቸው ከሚገኙበት ቦታ ጋር ለመመሳሰል ይረዷቸዋል፣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ፓተሮኖች እንስሳትን ውብ ሆነው እንዲታዩ ይረዷቸዋል** ብለው ይንገሩት።
- **የእንስሳት ስዕልን ከፓተርናቸው ጋር ያዛምዱ።** ለልጅዎ ገለጻ ያድርጉለት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት። ከዚያም **እንስሳ ብትሆን የትኛውን ፓተርን ትመርጣለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- *በአማራጭነት - ልጅዎ እንስሳ ሊመርጥ እና ከነ ፓተርኑ ሊስለው ይችላል። ለጅዎ በተጨማሪም እንስሳ ሊሰራና አዲስ ፓተርን ሊፈጥርለት ይችላል።*


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 8

## ማንበብና መጻፍ፥ የድምጽ ቀለሞችን መለያየት

- ለልጅዎ **እስኪ ቃላትን በድምጽ ቀለማቸው እንለያያቸው** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **እስኪ giraffe የሚለውን ቃል ድምጾች አንድ ላይ እናገናኝ። Gi** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **raffe። giraffe የሚለው ቃል ስንት የድምጽ ቀለሞች አሉት? አዎ፡ 2! Gi-raffe፣ gi-raffe** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግ የአንተ ተራ ነው። lion** (li-on) **የሚለውን ቃል የድምጽ ቀለሞች ለያይ** ብለው ይ ንገሩት። ሙከራውን በNolan (No-lan) ደግማችሁ ስሩ።
- ልጅዎ እርዳታ ቢፈልግም ገና እየተማረ ስለሆነ ምንም ማለት አይደለም!
- ልጅዎ ይህን በቀላሉ መስራት ከቻለ የራሱን ባለሁለት ድምጽ ቃላት እንዲያስብ መጠየቅ ወይም የሚሞክረው ባለ ሶስት የድምጽ ቀለም ቃል (el-e-phant, sa-van-na, sa-fa-ri) ሊሰጡት ይችላሉ።

## ያንብቡ፥ የዱር እንስሳት ማቆያ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *የዱር እንስሳት ማቆያ*

- ልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የዱር እንስሳት ማቆያ/ The Zoo* መጽሀፍን አንብቡ። በምታነቡበት ወቅት በገጽ 7 ላይ ያለውን አደንቀጽ ጠቁመው ያሳዩት እና **አንቀጹ በዱር እንስሳት ማቆያው ውስጥ ስንት የሜዳ አህያዎች፣ ዝሆኖች እና አንበሶች እንዳሉ ይነግረናል። በማቆያው ውስጥ አንድ የሜዳ አህያ፣ ሁለት አንበሶች እና ሶስት ዝሆኖች አሉ። ትልቁ መስመር በዱር እንስሳት ማቆያው ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘውን እንስሳት ይነግረናል** ብለው ይንገሩት።
- **በዱር እንስሳት ማቆያው ውስጥ ብዙ ቁጥር ያለው እንስሳ የትኛው ነው?** ብለው ይጠይቁት። ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገው እንኳ ገና እየተማረ ስለሆነ ምንም ማለት አይደለም።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ የሊሊ ፓድ ዝላይ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ማጣበቂያ፣ በሊሊ ፓዶች ቅርጽ የተቆረጠ ወረቀት፣ እያንዳንዱን ሊሊ ፓድ ከ0-3 መለያ ቁጥር በመስጠት ልጅዎ እንዲዘለቸው ለማስቻል በደፈናው ወለል ላይ በማጣበቂያ ያጣብቋቸው**



- ለልጅዎ **እስኪ እንደ ትናንሽ እንቁራሪት እንሁንና በሊሊ ፓዶቻችን ላይ እንዝለል** ብለው ይንገሩት።
- **እኔ ቁጥር ስጠራ አንተ ደግሞ ቁጥሩን ትዘለዋለህ** ይበሉት።
- ልጅዎ ቁጥር እንዲጠራ ናዎቻችሁን ተቀያየሩ። በተጨማሪም ማን ቀድሞ እንደሚደርስ ለማየት ተመሳሳይ ቀጥር ላይ በመዝለል መወዳደር ትችላላችሁ።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ የእንስሳት ቡችሎች


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ቀለም ወይም ከለር መቀቢያዎች፣ ብችላዎች መስሪያ ቁሳቁሶች - ለምሳሌ፡ የወረቀት መጠቅለያዎች፣ ያረጁ ካልሲዎች፣ ቡናማ የወረቀት ቦርሳዎች፣ ማጣበቂያ፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች፣** ***በአማራጭነት - እንደ አይን መቀቢያዎች ወይም የቆዳ ክሮች የመሳሰሉ የማስዋቢያ ቁሶች***





- ለልጅዎ **እስኪ አንድ ላይ ሆነን የእንስሳት ቡችሎች እንስራ። ምን እንስሳ መስራት ይኖርብናል?** ብለው ይጠይቁት። እውነተኛ እንስሳ መስራት ወይም አንድ ላይ ሆናችሁ አዲስ እንስሳ መፍጠር ትችላላችሁ።
- ባሏችሁ ቁሳቁሶች ተጠቅማችሁ የእንስሳ ቡችላ ስሩ። ለምሳሌ፡ የወረቀት መጠቅለያዎችን ማስዋብ ወይም ቡናማ የወረቀት ቦርሳውን ከስር እጃችሁን በምትከቱበት ወቅት አይጥ ዘላ ስትወጣ አስመስላችሁ መስራት፣ ወዘተ
- ከዚያም ለልጅዎ ከቡችሎች ጋር መጫወት እና እንስሳቱ የሚያደርጓቸውቸውን የተለያዩ ነገሮች አስመስለህ መስራት ትችላለህ ብለው ይንገሩት።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።










©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።









©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 9

## STEM: ከአካባቢያችን ጋር መመሳሰል


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [እንስሳት](), *በአማራጭነት - ወረቀትና ከለር መቀቢያዎች*

- ለልጅዎ **አንዳንድ እንስሳት ለመደበቅ ወይም ካሉበት አካባቢ ጋር ለመመሳሰል ቆዳቸውን ይጠቀማሉ። ይህን የሚያደርጉት ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? አዎ፡ ሊፋለሟቸው ወይም ሊበሏቸው ከሚፈልጉ ጠላቶቻቸው ለመደበቅ ነው** ብለው ይንገሩት።
- የውሀ ውስጥ እንስሳት ስዕሎች ያሳዩት - በዛጎል ውስጥ ያለ አሳ፣ ከአሸዋ በላይ ያለ አሳ እና በሳሻና የሚገኝ ቀጭኔ። **እነዚህ ሁሉም እራሳቸውን ከአካባቢያቸው ጋር ያመሳስላሉ።**
- **እንደ እስስት ያሉ አንዳንድ እንስሳት ቀለማቸውን ከሚገኙበት ቦታ ቀለም ጋር አመሳሰለው መቀየር ይችላሉ።**
- *በአማራጭነት - እንደ ቅጠል ወይም ዛፍ ያለ የተክል ስዕል ስለው ይቀቡ። ልጅዎ በቅጠሉ ወይም ዛፉ ላይ ተመሳሳይ ቀለም ያለው እንስሳ ሊስል ይችላል። ከልጅዎ ጋር እንስሳት ቀለማቸውን ከአካባቢያቸው ጋር ሲያመሳስሉ መለየት ምን ያክል ከባድ እንደሆነ ተነጋገሩ።*

## በግል መማር፥ መመሳሰል

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [መመሳሰል]()**፣ ከለር መቀቢያዎች ወይም ውሀማ ቀለም ጥቅል፣ ወረቀት**


- ለልጅዎ **ቀደም ብለን እንስሳት እራሳቸውን ከመኖሪያ ወይም የሚገኙበት አካባቢ ጋር ለማመሳሰል ቀለም እንደሚጠቀሙ ተነጋግረናል** ብለው ይንገሩት።
- **ለእንስሳት መመሳሰል እንዲረዳህ ይህን የዛጎል እና አሳ ስዕል ቀለም መቀባት ትችላለህ። አሳው እራሱን ከዛጎሉ ቀለም ጋር ለማመሳሰል ከፈለገ ይትጠቀመው ተመሳሳይ ነው ወይስ የተለያየ ቀለም? አዎ፡ ተመሳሳይ ቀለም** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሉን ቀለም እንዲቀባ ይፍቀዱለት። የተለያዩ ቀለሞችን ቢመርጥም ምንም ማለት አይደለም።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ስዕልህ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

## ማንበብና መጻፍ፥ በስዕሉ ላይ ምን እየተከሰተ ነው?

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*የዱር እንስሳት ማቆያ/The Zoo*]




- ለልጅዎ የዱር እንስሳት ማቆያ/*The Zoo.* መጽሀፍን ገጽ 4-5 ያሳዩት።
- ከዚያም **በዚህ ገጽ ላይ ምን ትመለከታለህ?** ብለው ይጠይቁት።
- ልጅዎን ተጨማሪ ዝርዝሮችን እንዲጨምር ለመስቻል የክትትል ጥያቄዎችን ሊጠይቁት ይችላሉ፤ ምሳሌ: **የሜዳ አህያው የት እንደሚገኝ ልትገልጽልኝ ትችላለህ? ስንት ዝሆኖች ይታዩሀል?**
- ከዚያም ስለተማረው ስለ እያንዳንዱ እንስሳ በተመለከተ አንድ ወይም ሁለት ነገር እንዲገልጽልዎ ይጠይቁት፤ እስካሁን የሜዳ አህያ ፈጠን እንደሆነና ዝሆን በኩንቢው ውሀ እንደሚጠጣ ተምሯል።

## የጆርናል ሙከራ፥ በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር መቀቢያዎች፣ እርሳስ፣ በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳት የጆርናል ገጽ**




ስም፥ ________________

በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳትን መጠበቅ ስለምንችልበት መንገድ ጻፉ።

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በመጥፋት ላይ ስላሉ እንስሳት እና ምን ያክል በቁጥር ጥቂት ብቻ በአለም ላይ እንደቀሩ ተነጋገሩ። አንዳንድ ጊዜ እንስሳቱ የሚጠፉት መኖሪያ ቦታቸው በሰው ልጆች ስለሚቃጠል ወይም በብክለት ምክንያት ነው።
- እንስሳትን መርዳት ስለሚቻልባቸው ሁለት መንገዶች ተነጋገሩ፤ ለምሳሌ: መኖሪያ ቦታቸውን ጠብቀን ለመቆየት ያስችለን ዘንድ የምንጠቀምባቸውን ነገሮች መልሰን መጠቀምና መቀነስ፣ የፕላስቲክ አጠቃቀም መቀነስ እና ሌሎች ሰዎችን እንስሳትን ስለ መርዳት ማስተማር።
- ልጅዎ በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳትን መርዳት ስለሚችልበት መንገድ እራሱን ችሎ እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳትን መርዳት ስለምትችልባቸው መንገዶች ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳትን መጠበቅ ስለምንችልበት መንገድ ጻፉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 10

## STEM: የተለያዩ አእዋፋት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የተለያዩ አእዋፋት]፣ ከለር መቀቢያዎች፣ ለህጻናት ተስማሚ መቀሶች**




- ለልጅዎ **በዚህ ገጽ ላይ ምን ያክል ወፎች እንዳሉ ቁጠር** ብለው ይንገሩት።
- **አእዋፋቱን ቀለም መቀባትና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ** ይበሉት። ልጅዎን እንደ አስፈላጊነቱ ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት።
- ከዚያም ልጅዎን ከ5 በላይ አእዋፋትን የማይይዙ የተለያዩ ምድቦችን እንዲሰራ ይጠይቁት፤ ለምሳሌ፡ 5 አእዋፋትን የሚይዝ ምድብ ስራ፣ አሁን ደግሞ 3 የተለያዩ አእዋፋትን የሚይዝ ምድብ ስራ።

## በግል መማር፥ የሳቫናና የደን እንስሳትን መለየት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [እንስሳት]: ለደን እና የሳቫና እንስሳት ካርዶችን ቆርጠው ያውጡ**

የቴምፕሬት ጫካ እንስሳት (FE)




- ለልጅዎ በሳቫናና በደን ስለሚኖሩ እንስሳት ለመንገር የስእል ካርዶቹን ይጠቀሙ።
- ለልጅዎ **እስኪ ስዕሎቹን ለይተን እናስቀምጥ። በሳቫና የሚኖሩ እንስሳትን በአንድ ምድብ ስር እና በደን የሚኖሩ እንስሳትን በሌላ ምድብ ስር አድርገህ አስቀምጥ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት። ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገውም ምንም ማለት አይደለም። ይህን መረጃ ወደ ውስጡ ማዋሀድ አይጠበቅበትም።
- ከዚያም **የደን እንስሳትን ወይስ የሳቫና እንስሳትን ማየት ትመርጣለህ? ለምን?** ብለው ይጠይቁት



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# አርብ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 2 ቀን 10

## ማንበብና መጻፍ፥ እስኪ ስለ ሳቫና እና እና ስለ ደን እንነጋገር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [እንስሳት]

- ለልጅዎ **በሳቫና እና በቴምፕሬት ደን ውስጥ ስለሚኖሩ እንስሳት ስንማር ቆይተናል** ብለው ይንገሩት። **ሳቫና ምንድን ነው? የቴምፕሬት ደን ምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት። አስፈላጊ ከሆነ ለልጅዎ ሳቫና በአፍሪካ የሚገኝ በአብዛኛው ሞቃት የሆነ ለጥ ያለ መሬት እንደሆነና የቴምፕሬት ደን ደግሞ ዛፎችን የያዘና የተለያዩ ወቅት ያሉት እንደሆነ ሊያስታውሱት ይችላሉ።
- ልጅዎን ከ2-3 የክትትል ጥያቄዎች ይጠይቁት፤ ለምሳሌ: **በሳቫና እና በደን ውስጥ ምን አይነት እንስሳትን ልናገኝ እንችላለን?** ወይም **የትኛውን መኀብኘት ትፈልጋለህ? ለምን?** የሀሳብ መለዋወጫ ውይይት ማድረግን ተለማመዱ።
- ልጅዎ ስለዚህ ርዕሰ ጉዳይ መነጋገር የማይፈልግ ከሆነ በምትኩ ስለ ምን ለመነጋገር እንደሚፈልግ ለጠይቁት ይችላሉ።




የሳቫና እንስሳት (FE)

## ያንብቡ፥ የዱር እንስሳት ማቆያ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*የዱር እንስሳት ማቆያ /The Zoo*]

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *የዱር እንስሳት ማቆያ/The Zoo* መጽሀፍን ያንብቡ።
- ከዚያም ገጽ 9ን ያሳዩት እና ህጎቹን ይመርምሩ። ቀጥለውም **አንበሳን ማላመድ የማንችለው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 3


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 7 ሳምንት 3 ምልከታ

## የውሀ ውስጥ እንስሳት



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በውሀ ውስጥ ስለሚኖሩ እንስሳት ይማራል እንዲሁም በጨዋማ ውሀና ንጹህ ውሀ ላይ የምርምር ሙከራ ያደርጋል። ልጅዎ ጥንድ ቃላትን እና የተለያዩ የውሀ ውስጥ እንስሳትን ይሰራል፣ እስከ 10 ድረስ ይቆጥራል፣ ከ0-3 ያሉ ቁጥሮችን ለይቶ ያውቃል፣ መስራት ስለሚችላቸው ነገሮች ይናገራል እንዲሁም መመሪያዎችን መከተልን ይለመመዳል። ለልጅዎ ሰልፍ ላይ እያለህ፣ አውቶቡስ በምትጠብቅበት ወቅት፣ ምግብ እስከሚዘጋጅ በምትቸጠብቅበት ወቅት፣ ወዘተ እስከ 10 መቁጠር ትችላለህ ብለው ይንገሩት። በተጨማሪም ልጅዎን መመሪያዎችን እንዲከተል በማድረግ ላይ ሊረዱት ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡ እስኪ ሸሚዞችህን ቀጥለህም ሱሪዎችህን እጠፋቸው።



### ቁልፍ ቃላት



**እንስሳ**

ልጆች ያሏቸው፣ ምግብ፣ ውሀና አየር የሚያስፈልጋቸው፣ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት መንቀሳቀስ የሚችሉ እና የተለያዩ የአካል ክፍሎች ያሏቸው ህይወት ያላቸው ነገሮች ናቸው።



**ዛጎል**

ዛጎል ተብሎ በሚጠራ ህይወት ያለው ፍጡር የሚፈጠር የጠንካራ አለቶች መስመር ነው።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለ ውሀ ውስጥ እንስሳት ትማራላችሁ። መርሀግብሩን ከመጀመራችሁ በፊት በውሀ ውስጥ የሚኖር እንስሳ ወይስ በምድር ላይ የሚኖር እንስሳ መሆን እንደሚመርጡ በተመለከተ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ።

## ያስቡበት!


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ




## **STEM:** እስኪ እስከ 10 እንቁጠር

- ለልጅዎ **እስኪ በእንስሳት ድምጾች በማስመሰል እስከ 10 እንቁጠር። ዝንጀሮዎች ምን አይነት ድምጽ ያወጣሉ?** ብለው ይጠይቁት።
- ተጨማሪ ከ1-2 ጊዜያት ቁጠሩ። ልጅዎን ድምጾች እንዲመርጥ ይፍቀዱለት፤ ለምሳሌ፡ እንደ ውሀ ውስጥ አሳ ወይም እንደ አይጥ ሲጥ ሲጥ ማለት
- ከዚያም **እስኪ አሁን በአሳ ድምጽ እስከ 7 ቁጠር። አሁን ደግ እስኪ አንደ አይጥ ሲጥ ሲጥ የሚል ድምጽ በመጠቀም እስከ 9 እንቁጠር** ብለው ይንገሩት። ልጅዎን ለመቁጠር በ0 እና 10 መካከል የሚገኙ የተለያዩ ቁጥሮችን እንዲመርጥ ይፍቀዱለት። በተጨማሪም በምትቆጥሩበት ወቅት የእንስሳት እንቅስቃሴዎችን ልትሰሩ ትችላላችሁ፣ ለምሳሌ፡ እንደ አሳ መዋኘት

## በግል መማር፥ የጨው አርት እንስሳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ጨው፣ ፈሳሽ ማጣበቂያ፣** [ሲሆርስ]**፣ ወይም ወረቀትና ከለር መቀቢያዎች**

- ለልጅዎ **ዛሬ ጨው እና ማጣበቂያ በመጠቀም አርት ትሰራለህ። ማጣበቂያውን የሲሆርስ ስዕል ላይ ልታደርገውና ከዚያም ጨው ልታጣብቅበት ትችላል** ብለው ይንገሩት። ማጣበቂያውን እንዴት ስዕሉ ላይ ቀስ ብሎ ማጣበቅ እንደሚችል ያሳዩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ተግባሩን እንዲያጠናቅቅ ይፍቀዱለት። ልጅዎ የራሱን እንስሳ ስሎ ሊያጣብቅና ጨው ሊነሰንስበት ይችላል።
- ከዚያም **ይህን እስኪደርቅ ልንተወው እና ነገ ልንቀባው** እንችላለን ብለው ይንገሩት




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ




## ማንበብና መጻፍ፥ ተራ መመሪያዎች

- ለልጅዎ **እንድትከተላቸው የምፈልጋቸው ተራ መመሪያዎችን እሰጥሀለሁ። በጥንቃቄ አዳምጠኝ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ተራ ባለ ሁለት ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት: የሞኝ ፊት አሳይና ቀጥለህም የዝንጀሮ ድምጽ አውጣ፣ ልክ እንደ ፔንጊዩን እየተራመድክ ክንፎችህን አርገብግብ፣ ወዘተ
- ልጅዎ መመሪያዎችን እንዲሰጥዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## ያንብቡ፥ ጫማዎቼን ማሰር

ጫማዎቼን
ማሰር
ደራሲ Julie Fowier
ሰዐሊ Kennedy White





**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *ጫማዎቼን ማሰር*

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው *ጫማዎቼን ማሰር/ Tying My Shoes* ምንባብን አንብቡ።
- ከዚያም **ቦቢ ጫማዎቹን ለማሰር የተቻለውን ያክል ሙከራ አድርጓል። የተቻለህን ያህል ለማድረግ የሞከርክበት ምን አዲስ ነገር አለ? ይህን ነገር ስታደርገው ምን አይነት ስሜት ተሰማህ?** ይበሉት።

በተጨማሪም የዚህን መጽሀፍ በቅድሚያ የተቀዳ ንባብ ከSpakler መተግበሪያ ላይ “ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች” ክፍል፡ የእንስሳት ግዛት ከሚለው ስር ማግኘት ይችላሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ሲሆርስ (FE)

# ማክሰኞ



## STEM: በጨዋማ ውሀ እና በንጹህ ውሀ መንሳፈፍ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ 2 ብርሀን የሚያሳልፉ ኩባያዎች ወይም ብርጭቆዎች፣ ውሀ፣ ጨው፣ ማንኪያ፣ እንቁላል (እንቁላል ከሌላችሁ ከለር መቀቢያ ወይም የተወሰነ ቀላል ክብደት ያለው ነገር ይጠቀሙ)**

- ለልጅዎ **እስኪ ልክ እንደ ውቂያኖስ ያለ ጨዋማ ውሀ እና እንደ ሀይቅ ያለ ንጹህ ውሀ ለመማር ሙከራ እንስራ** ብለው ይንገሩት።
- ከዚያም **በንጹህ ውሀ ውስጥ ያለው እንቁላል ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ?** ብለው ይጠይቁት። እንቁላሉን በንጹህ ውሀ ውስጥ ይክተቱ። ከዚያም ልጅዎን **እንቁላሉ ላይ ምን ተፈጠረ? አዎ: እንቁላሉ ሰምጧል። እንቁላሉ በንጹህ ውሀ ላይ ይንሳፈፋል** ይበሉት።
- **እዚህ ውሀ ውስጥ ጨው ጨምረን ከዚያም እንቁላሉን ብንጨምርበት ምን ይሆናል ብለህ ታስባለህ?** ልጅዎን በውሀው ውስጥ ሙሉ ማንኪያ ጨው ይጨምሩበትና ይበጥብጡት። ከዚያም እንቁላሉን ይጨምሩ።
- ከዚያም **በእንቁላሉ ላይ ምን ተፈጠረ? አዎ እንቁላሉ ተንሳፈፈ!** (እንቁላሉ የማይንሳፈፍ ከሆነ ተጨማሪ ጨው ይጨምሩ)። **ጨዋማ ውሀ ጥቅጥቅ ወይም ከባድ በመሆኑ ምክንያት እና ይህም ከመዋኛ ገንዳ ይልቅ በሀይቅ ላይ መንሳፈፍን ቀላል ስለሚያደተርገው ለነገሮች መንሳፈፍ ቀላል ነው።**

## በግል መማር፥ የጨው አርት እንስሳትን መቀባት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከቀዳሚው ቀን የተወሰደ የጨው እንስሳ አርት፣ ውሀማ ቀለም ጥቅል**

- ለልጅዎ **ትናንትና የጨው እንስሳት ሰርተሀል። ዛሬ እንስሳውን መቀባት ትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ከመቀባትዎ በፊት ከልጅዎ ጋር አርት ምን እንደሚመስል ምን ስሜት እንደሚሰጥ ይንጋገሩ። ቀለም ቅቡ በጣም ውሀ የበዛበት ስለመሆኑ፣ ጨዉ በውሀው ውስጥ ስለመሟሟቱ ይነጋገሩ። ልጅዎ በዝግታ ጨዉን በመንካት ወይም ቡርሹን በጨዉ ላይ በማጣበቅ መቀባት አለበት። ለልጅዎ ገለጻ ያድርጉለት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስዕሉን እንዲቀባ ይፍቀዱለት።
- ከዚያም **እስኪ ስለ ቀለም ቅብህ ንገረኝ** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ



## ማንበብና መጻፍ፥ ማድረግ የምችለው አዲስ ነገር!


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ልጅዎ በቀን 3 መስራት ስለሚችላቸው ነገሮች የተመለከተ ዝርዝር፣ ከለር መቀቢያዎች**

- ዝርዝሩን ከልጅዎ ጋር ማድረግ ዘስለሚችላቸው ነገሮች ለመነጋገር ይጠቀሙበት። ዚያም **ይህን ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ዝርዝር መጀመሪያ ስለ ስለ እንስሳት መማር ስንጀምር አዘጋጅተሀል** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን በዚህ ዝርዝር ውስጥ መጨመር የምትችለው ማድረግ የምትችለው ተጨማሪ ነገር ምንድን ነው?** ለልጅዎ ማድረግ ስለሚችላቸው ነገሮች እንዲያስብ ይርዱት፤ ለምሳሌ፡ በራሳቸው ውሀ ውስጥ መጨመር፣ እስከ 10 መቁጠር ወይም በቤት ውስጥ ስራዎች ላይ መርዳት
- ልጅዎን ማድረግ የሚችላቸው ተጨማሪ ነገሮችን በዝርዝሩ ውስጥ እንዲካትት ይፍቀዱለት።

## የጆርናል ሙከራ፥ የውሀ ውስጥ እንስሳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለር መቀቢያዎች ፣ እርሳስ፣ የውሀ ውስጥ እንስሳ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር አንድ ላይ ሆነው በውሀ ውስጥ ስለሚኖሩ እንስሳት ተነጋገሩ።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ስለሚወደው ውሀ ውስጥ የሚኖር እንስሳት እንዲስልና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ቀጥለውም **እስኪ ስለምትወደው የውሀ ውስጥ እንስሳት ንገረኝ። ይህን እንስሳ ለምን ወደድከው?** ብለው ይጠይቁት።


ስም፥ ________________

ስለምትወዱት የውሃ እንስሳ ጽሁፍ ጻፉ እና ስዕል ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

ስለምትወዱት የውሃ እንስሳ ጽሁፍ ጻፉ እና ስዕል ሳሉ።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 3 ቀን 13

## STEM: 0-3


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እያንዳንዱን ከ0-3 ቁጥሮች ለእያንዳንዱ ቁጥር 2 የቁጥር ካርዶች ለማዘጋጀት በቁራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ**

- ለልጅዎ አንድ ካርድ ይስጡት እና ለራስዎ አንድ ካርድ ይያዙ።
- ለልጅዎ **እስኪ በቁጥሮች ጌም እንጫወት። የቁጥር ካርድ አሳይሀለሁ። አንተ የቁጥሩን ስም ትጠራልኝ እና ያንን ቁጥር የሚይዘውን ካርድ ተሳየኛለህ።**
- ልጅዎ እርስዎ ፈልገው የሚያገኙትን ካርድ እንዲያሳይዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።
- ይህን ተግባር ተጨማሪ ቁጥሮች በጨመር ወይም ልጅዎን በካርዱ ላይ ከሚገኘው ቁጥር ጋር ተመሳሳይ ብዛት ያላቸው ቁሶችን እንዲፈልግ በመጠየቅ የበለጠ ከባድ ማድረግ ይችላሉ።
- የቁጥር ካርዶቹን በቀን 16 ለሚሰሩ ተግባሮች ያስቀምጧቸው።

## በግል መማር፥ የውሀ ውስጥ እንስሳት እንቆቅልሽ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ [የውሀ ውስጥ እንስሳት እንቆቅልሽ]፣ ከለሮች፣ መቀሶች፣** ***በአማራጭነት - ስዕሎቹን በካርቶን ላይ ያጣብቁ፣ ምሳ፡ ቆርጠው ከማውጣትዎ በፊት የጥራጥሬ ሳጥኖች***

- ለልጅዎ **እነዚህን የውሀ ውስጥ እንስሳት ስዕሎች ቀለም መቀባት ትችላለህ። ከዚያም ቁርጥራጮችን መስራት እና አንድ ላይ መገጣጠም ገትችላለህ** ብለው ይንገሩት።
- ልጅዎን እራሱን ችሎ ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ። ከዚም ልጅዎን እራሱን ችሎ ቁርጥራጮቹን መገጣጠም እንዲችል ቆርጦ በማውጣት ላይ ይርዱት። ከዚያም **ከውሀ በታች ስዕሉ ውስጥ ስለምታያቸው እንስሳት ንገረኝ** ብለው ይጠይቁጥ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 3 ቀን 13

## ማንበብና መጻፍ፥ ጥንድ ቃላትን መመስረት እችላለሁ

- ለልጅዎ **ሁለት ቃላትን እነግርህ እና ከዚያም ቃላቱን አንድ ጥንድ ቃል ለመመስረት አንድ ላይ ታገናኛቸዋለህ** ብለው ይንገሩት።
- **ሁለቱ ቃላት እነዚህ ናቸው: "hair"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **"brush"። ሁለቱን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸዋለሁ ማለትም hair** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **brush፤ hairbrush** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግሞ የአንተ ተራ ነው። እስኪ እነዚህን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸው: "sail"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **"boat"፣ sail** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **boat።** ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገውም ገና በመማር ላይ ስለሆነ ምንም አይደለም። ልጅዎን ለሙከራው ያሞግሱት እና ቃላቱን ደግመው ይናገሯቸ ። ከዚያም ጥንድ ቃሉን መልሰው ይናገሩ። **በጥንቃቄ አስብ! አንድ ላይ sailboat የሚለውን ቃል ለመስራት Sail** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **boat።**
- ሙከራውን shoebox እና strawberry በሚሉት ቃላት ደግመው ይስሩ።


## ያንብቡ፥ ጫማዎቼን ማሰር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*ጫማዎቼን ማሰር*]

- ከልጅዎ ጋር በመሆን፣ *ጫማዎቼን ማሰር* የሚለውን መጽሃፍ አንብቡ።
- ከዚያ በኋላ፣ ገጽ 8-9 ያሳዩት። ይህንን ይበሉት፣ **ቦቢ መጀመሪያ ላይ ጫማውን ማሰር ሲያቅተው ተበሳጭቶ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ነገሮች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ ሁላችንም እንበሳጫለን።**
- **የመደናገጥ ስሜት ሲሰማህ ምን ማድረግ ትችላለህ?**
- እንዲሁም፣ በስፓርክለር/ Sparkler መተግበሪያ ላይ “ተጫወት” በሚለው ክፍል ውስጥ “ማረጋጊያ” እንቅስቃሴዎችን መመልከት ይችላሉ።

ጫማዎቼን ማሰር

ደራሲ Julie Fowier
ሰዐሊ Kennedy White





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ




## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ስብስቦችን መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከአንድ ቤት የሚገኙ 5 እቃዎች፣ ምሣሌ 5 የተድበለበሉ ካልሲዎች ወይም 5 ባለቀለም እርሳሶች**

- እንዲህ ይበሉ፡ **ስብስቦችን ይዘን ጨዋታ እንጫወታለን። እኔ የአንተ ስብስብ ስንት እቃዎችን እንደሚይዝ እነግርሃለሁ። አንተ ደግሞ የሚያስቁ አካሔድ በመሔድ እቃዎቹን ትሰበስባለህ።**
- የተለያዩ መመሪያዎችን ይስጡ፡ ለምሣሌ፡ እየዘለልን 2 የካልሲ ስብስብ እንሰራለን፣ ወደከለሮቹ እየተወዛወዝን በመሔድ 4 ባለቀለም እርሳሶች ስብሰብ እንሰራለን፤
- ልጅዎ መመሪያዎችን ለእርስዎ መስጠት እንዲችል ሚናዎቻችሁን ተቀያየሩ።


## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ በዛጎላማው ድንጋይ አካባቢ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** **[በዛጎላማው ድንጋይ አካባቢ]** ለልጆች የማያሰጋ መቀስ




- እንዲህ ይበሉት፣ **በድንጋያማ የውሃ ዳርቻ ነን ብነህ አስብ። ጎቢ አሳ እና ፒስቶል ሽሪምፕ የተባሉ እንስሳት እርስ በእርስ ይረዳዳሉ ምክንያቱም ፒስቶል ሽሪምፕ በደንብ አጥርቶ ማየት ይችላል፣ ግን መቆፈር ይችላሉ። ጎቢ ፊሽ ደግሞ አከባቢውን ከጠላቶች ወይም አዳኞች ይከላከላል፤ እናም ፒስቶል ሽሪምፕ ቤት ሲሰራ ጠላቶችን ለማባረር የሚችል ጮኽ ያለ ድምጽ ያሰማል።**
- **እንስሳትን በቀለም ማሳመር እንችላለን። እንግዲህ እስቲ ቀርጸን እናውጣቸው እና አሁን ያሉት በድንጋያማ ወንዙ ወለል ውስጥ እንደሆኑ እናስብ።** እንስሳቶቹን ቀርጻችሁ ካወጣችሁ በኋላ እየተጫወታችሁ የተለያዩ ትዕይንቶችን ስትፈጥሩ እንዲቆሙ እና እንዲዘዋወሩ ለማድረግ እጠፏቸው።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።






©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።












©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ



## STEM: በዛጎላማው የወንዙን ዳርቻ መገንባት





**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** መጫወቻ ጭቃ ወይም **[የመጨዋቻ ጭቃ አሰራር]**፣ **[እንስሳት]**፣ *እንደአማራጭ - ሰለስላሳ ወረቀት ወይም የመጸዳጃ ወረቀት ጥቅልል*


- ከልጅዎ ጋር፥ የበስልክ ወይም በታብሌት ላይ ድንጋያማ የውሃ ዳርቻ ምን እንደሚመስል ተመልከቱ። ወይም የውሃ አካላት ምስል ካለበት ምስል ላይ የዳርቻውን ምስል ተመልከቱ።
- እንዲህ ይበሉት: **ዛጎላማ/ድንጋያማ የውሃ ዳርቻ የሚባለው ልክ እንደ ትንሽዬዋ ኮራል ያሉ በርካታ እነስሳት የሚኖሩበት ሲሆን፣ አንድ ላይ ስብስብ ሲሉ የሚያማምሩ ድንጋይ ይመስላሉ። በርካታ አሳዎች እና ሌሎች እንስሳት በሌሎች ድንጋያማ የውሃ ዳርቻዎች መኖር ይመቻቸዋል።**

- **የእኛን መጫወቻ ጭቃ ተጠቅመን እስቲ ድንጋያማ የውሃ ዳርቻ እንገንባ።** አንድ ድንጋያማ መሰል የውሃ ዳርቻ ምን መልክ እንደሚኖረው በአንድነት በመነጋገር ኮራል የሚመስል ቅርጽ ፍጠሩ። በጭቃዎቹ ላይ ቀዳዳዎችን በመብሳት ኮራል እንዲመስሉ ማድረግ ትችላለችሁ።
- *እንደአማራጭ: ከመጫወቻ ጭቃ ይልቅ፥ አንድ ኢንች የሆኑ ቁራጮችን ከለስላሳ ወረቀቶቹ እና የመጸዳጃ ቤት ወረቀቶቹ ጠርዝ ላይ በመቅደድ በተለያዩ መልኮች እርስ በእርስ ማጣበቅ እና ቀለም መቀባት ትችላላችሁ።*

## በግል መማር፥ ለቦቢ የተጻፈ ደብዳቤ

ጫማዎቼን ማሰር

ደራሲ Julie Fowler
ሰዐሊ Kennedy White




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** *[ጫማዎቼን ማረር]*፣ ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ

- ከልጅዎ ጋር በመሆን *ጫማዎቼን ማሰር* ስለተባለው መጽሐፍ ያውሩ። እንዲህ ይበሉ: **ቦቢ ጫማውን ማሰር ባልቻለ ጊዜ በመጀመሪያ ላይ ተበሳጭቶ ነበረ። በሚችለው አቅም ሁሉ ጥረት ማድረጉን እንዲቀጥል እንዲበረታ የሚያደርግ ደብዳቤ ልትጽፍለት ትችላለህ።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ደብዳቤውን እንዲጽፍ እና ስዕል እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያም እንዲህ ብለው ይጠይቁ: **ለቦቢ ምን ብለህ ጻፍክ?**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሃሙስ



## ማንበብና መጻፍ፥ ዋና ገጸ ባህሪ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ***ጫማዬን ማሰር፣***

- ጫማዬን ማሰር የሚለውን መጽሃፍ ያሳዩትና እንዲህ ይበሉ፡ **ይህንን መጽሐፍ ስናነብ ቆይተናል፤ ዋናው ገጸባህሪ ማን ነው?**
- **አዎን፥ ቦቢ ነው። ይህ ታሪክ ስለቦቢ የሚያወራ ነው። ዋነኛው ገጸባህርይ እርሱ ነው። እናቱ ሌላኛዋ ገጸባህርይ ናት፤ ዳሩ ግን ታሪኩ በአብዛኛው የሚያወራው ስለቦቢ ነው።**
- **እስቲ ቦቢን እንግለጸው፤ ሰስለእርሱ ምን እናውቃለን?** ለልጅዎ ታሪኩን ፈጠን ብለው ለማስታወስ ከፈለጉ ምስሎቹን ገረፍ ገረፍ አድርገው ማሳየት ይችላሉ። አንዳንድ ምሣሌዎችን ይስጧቸው ለምሣሌ፥ ቦቢ ቀይ ሸሚዝ ነበረው ወይም ቦቢ መጀመሪያ ጫማውን ማሰር አልቻለም ግን ደጋግሞ ሲለማመድ ስለቆየ በስተመጨረሻ ተሳካለት።





**ጫማዎቼን**
ማሰር
ደራሲ Julie Fowier
ሰዐሊ Kennedy White

## የጆርናል ሙከራ፥ እኔ እንስሳ ነኝ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** ባለቀለም እርሳስስ/ከለሮች፣ እርሳስ፣ እኔ እንስሳ ነኝ የጆርናል ገጽ

- ከልጅዎ ጋር በመሆን ስለተለያዩ እንስሳት ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ለብቻው በመሆን እንስሳ ቢሆኑ ሰስለሚመርጡት ስለአንድ ስለሚወዱት እንስሳ እንዲጽፍ ያድርጉ።
- ከዚያም እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **መሆን የምትፈልገው እንስሳ ምን እንደሆነ ንገረኝ። ይህንን እንስሳ ለምን መረጥክ?**





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ _________________

እንስሳ መሆን ብትችሉ የትኛውን እንስሳ መሆን ትፈልጋላችሁ?



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## STEM: የውሃ ውስጥ እንስሳት ስብስብ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** **የሻርክ ስብስቦች**፣ ባለቀለም እርሳስ፣ ለልጆች የማስጋ መቀስ



- እንዲህ ይበሉ: **ሻርኮቹን ቀርጻችሁ አውጡ፤ የሻርክ ስብስብ ልንሰራ ነው፤ ግን መጀመሪያ፣ ቀለም በማቅለም ቆርጠን እናወጣቸዋለን።** ልጅዎ ሻርኮቹን ቀለም እንዲያቀልም በመፍቀድ፣ ቀርጾ በማውጣት ያግዙት።
- ከዚያም፥ ከ5 የማይበልጡ የሻርኮች ስብስብ እንዲሰሩ ያድርጉ፤ ለምሳሌ የ4 ሻርኮች ስብስብ ስራ፣ ወይም የ2 ሻርኮች ስብስብ ስራ።

## በግል መማር፥ የእኔ የውሃ ትዕይንት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የውሃ ቀለም መቀቢያ ወይም ባለቀለም እርሳስ፣ ወረቀት**

- ከልጅዎ ጋር በመነጋገር ወደሐይቅ፣ ወራጅ ወንዝ፣ ውቂያኖስ ወይም አኳሪየም በመሔድ የጎበኛችሁበትን ጊዜ ያውሩ። **የውሃ አካል ያለበት ብትሔድ ምን ማድረግ ትወዳለህ?**
- እንዲህ ይበሉት፣ **በውሃ አከባቢ ማድረግ ስለምትፈልገው ነገር አንድ ስዕል መስራት ትችላለህ።** ልጅዎ እራሱን ችሎ ምስል እንዲሰራ ያድርጉት።
- ከዚያም እንዲህ ይጠይቁት፣ **ስለሰራሃ ስዕል ንገረኝ። በውሃው ምን መስራት ትፈልጋለህ?**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ



## ማንበብና መጻፍ፥ መመሪያዎችን እየተከተልኩ ነው?

- እንዲህ ይበሉ፡ **እስቲ ጌም እንጫወት። እኔ የምከተለው ሁለት ትዕዝዛዝ ልትሰጠኝ ትችላለህ። ከዘያም አቅጣጫውን በትክክል እየተከተልኩ ከሆነ ንገረኝ ወይም ትክክል ካልሆንኩ ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ንገረኝ።**
- ልጅዎ ለእርስዎ አቅጣጫ እንዲመራ/ትመራዎት ይፍቀዱ። አብዛኛውን ጊዜ መመሪያዎቹን ይከተሉ ግን አንዳንዴ ይሳሳቱላቸው፤ ለምሣሌ፡ ፈንጠር ብለው በጣትዎ ድምጽ ከማሰማት ይልቅ ዘለል ብቻ ይበሉ፣ በዚህም ጊዜ ልጅዎ እርስዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት በተራው/ዋ ያሳይዎታል/ታሳይዎታለች። ካላስተካከሉዎት፥ መመሪያውን እንዳልተከተሉ ያስታውሷቸው።


## ያንብቡ፥ *ጫማዎቼን ማሰር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [*ጫማዎቼን ማሰር*]፣ ወረቀት እና ባለቀለም እርሳስ

- ከልጅዎ ጋር በመሆን *ጫማዎቼን ማሰር* የሚለውን መጽሃፍ ያንብቡ።
- ከዚያም እንዲህ ይጠይቁት፣ **ከዚህ ታሪክ ምን ታስታውሳለህ?** ልጅዎ በታሪኩ ውስጥ ከተከሰቱት ሁለት ነገሮችን እንዲያስታውስ ያበረታቱ።
- ከታሪኩ ላይ የሚያስታውሱትን ነገር በስዕል እንዲያስቀምጡ ወይም እንዲጽፉ ያድርጓቸው።


ጫማዎቼን
ማሰር

ደራሲ Julie Fowier
ሰዐሊ Kennedy White





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሳምንት 4


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ምልከታ


## የፕሪየር እንስሳት



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ፥

በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ሣምንት፥ ልጅዎ ስለዱር እና የቤት እንስሳት በመማር፥ ስለእንስሳቱ መኖሪያ አከባቢ፣ በመማር፣ የወፎችን ጎጆ መገንባት እንዲሁም የእንቁራሪቶችን ስብስብ መስራት ይማራል።

በአጎራባች አከባቢያችሁ በምትንቀሳቀሱበት ጊዜ የእንስሳትን መኖሪያ አከባቢ መፈለግ ትችላላችሁ። የወፎችን ጎጆ፣ የውሾችን ማደሪያ፣ የእርሻ እንስሳትን በረት ማግኘት ቻላችሁን?



### ቁልፍ ቃላት



## የቤት እንስሳት

ለሰዎች ስራ የሚሰሩ ወይም ቤት ውስጥ የሚሆኑ እንስሳት ናቸው



## መኖሪያ አከባቢ

እንስሳት የሚኖሩበት ቦታ



## የዱር እንስሳት

ማንም የሚቆጣጠራቸው ስለሌለ ባህርያቸው ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ በተፈጠሯቸው ውጭ የሚኖሩ እንስሳቶች ናቸው


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

ስለእንስሳት የምንማርበት የመጨረሻው ሣምንት ነው። ይህንን እሽግ ከመጀመራችን በፊት፥ ስለእንስሳት እስካሁን ስለተማርናቸው ነገሮች ጻፉ ወይም ስዕል ሣሉ።

**ያስቡበት!**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## **STEM:** ከ0-3 ፍሪዝ ዳንስ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ሙዚቃ፣ 0-3 በቁጥር ያለባቸው የ13ኛው ቀን ካርዶች**

- የቁጥር ካርዶችን በመውሰድ በወለል ላይ በተለያዩ ቦታዎች ያስቀምጧቸው።
- እንዲህ ይበሉ፡ **ቁጥሮቻችንን በመጠቀም ፍሪዝ ዳንስ ልንጫወት ነው።** በወለል ላይ ያሉትን ቁጥሮች እስቲ በጋራ እንጥራ።
- እንዲህ ይበሉ፡ **ሙዚቃ ሲከፈት መደነስ ትችላለህ። ልክ ሙዚቃው ሲቆም፣ አንድ ቁጥር እጠራለሁ። ከዛም እዚያ ቁጥር ዘንድ ቶሎ በመሔድ ቀጥ ብላህ ትቆማለህ።**
- ጥቂት ዙር ተጫወቱ እና ልጅዎ ደግሞ በተራው እርስዎ ሮጠው የሚያገኙትን ቁጥር እንዲጠራ ያድርጉ።
- ልጅዎ ዝግጁ ሲሆን፣ ተጨማሪ ወይም ሌሎች ቁጥሮችን መጨመር ይችላሉ።

## በግል መማር፥ የዱር ወይም የቤት እንስሳት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** [የቤት እንስሳት] ተቆርጦ የተዘጋጀ፣ የሳቫና እንስሳት ተቆርጠው የሚወጡባቸው የእንስሳት ካርድ

- የሳቫና እንስሳትን እና የቤት እንስሳትን ምስል በመጠቀም፣ ስለቤት እንስሳት እና ስለዱር እንስሳት ይናገሩ። እንዲህ ይበሉ፡ **የዱር እንስሳት የሚኖሩት በተፈጥሯዊ አካባቢ ውስጥ ነው እናም ከሰዎች እርዳታን አያገኙም። የዱር እንስሳት ለመጫወቻ አይሆኑም። የቤት እንስሳት የሚኖሩት በእርሻ ወይም በሰዎች ቤት ነው። ምስሎቹን እስቲ የቤት እንስሳ እና የዱር እንስሳ አድርገን እንደርድራቸው።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ስዕሎቹን እንዲለዩ ያድርጉት። እርዳታ የሚፈልግ ከሆነ ምንም ችግር የለውም፣ ገና ለመማር እየሞከረ ነው። እንደ አህያ ያሉ አንዳንድ እንስሳት በሁለቱም ምድብ ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ፣ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ እንደ ቤት እንስሳ ተደርገው ይታሰባሉ።
- በደንብ አድናቆት ይስጡት። **በጣም ምርጥ ስራ ነው! በጥንቃቄ እያሰቡ ሲሆን የተቻለህን ያህል ለመስራት እየሞከሩ ነው!**



የቤት እንስሳት (FE)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሰኞ



## ማንበብና መጻፍ፥ እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት

- ለልጅዎ **እስኪ ጥንድ ቃላትን እንመስርት** ብለው ይንገሩት
- **እኔ ሁለት ቃላትን እነግርህና አንተ ደግሞ አንድ ጥንድ ቃል ለመመስረት ቃላቱን አንድ ላይ ታገናኛቸዋለህ** ይበሉት።
- **ሁለቱ ቃላት እነዚህ ናቸው: " blue"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **" berry"። ሁለቱን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸዋለሁ ማለትም blue** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **berry፣ blueberry** ብለው ይንገሩት።
- **አሁን ደግሞ የአንተ ተራ ነው። እስኪ እነዚህን ቃላት አንድ ቃል ለመፍጠር አንድ ላይ አገናኛቸው: "shoe"** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **" box"፣ shoe** (ትንፋሽ ይውሰዱ) **box።** ልጅዎ እርዳታ ቢያስፈልገውም ገና በመማር ላይ ስለሆነ ምንም አይደለም። ልጅዎን ለሙከራው ያሞግሱት እና ቃላቱን ደግመው ይናገሯቸው ። ከዚያም ጥንድ ቃሉን መልሰው ይናገሩ። **በጥንቃቄ አስብ! አንድ ላይ shoebox የሚለውን ቃል ለመስራት** Shoe (ትንፋሽ ይውሰዱ) **box።**
- ሙከራውን cowboy እና sunshine በሚሉት ቃላት ደግመው ይስሩ።

## ያንብቡ፥ *Count the Noisy Birds/ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Count the Noisy Birds/ ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር*

- ከልጅዎ ጋር ብረው *ሆነው ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር* የሚለውን መጽሃፍ እያነበባችሁ ሳሉ አብራችሁ ቁጠሩ።
- ከዛ በኋላ፣ ገጽ 22-23 ያሳዩት እና ልጅዎን እያንዳንዱን የወፎች ስብስብ እንዲቆጥር ያድርጉት።

በተጨማሪም የዚህን መጽሀፍ በቅድሚያ የተቀዳ ንባብ ከSpakler መተግበሪያ ላይ "ለአዋቂዎች የቀረቡ ፍንጮች" ክፍል፡ የእንስሳት ግዛት ከሚለው ስር ማግኘት ይችላሉ።





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።














©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ቀን 17

## STEM: የወፍ ሕይወት ዑደት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የወፍ ሕይወት ዑደት፣ ለልጆች የማያሰጋ መቀስ፣ ማርከሮች፣ ወረቀት፣ ማጣበቂያ፣ *በአማራጭነት - እንቆቅልቹን ካርቶኑ ላይ ያጣብቁት፣ ለምሳሌ፣ ከመቀባታችሁ በፊት የእህል ሳጥኑን ቀለም ቀቡት***


- ይህን ይበሉት፣ **የሕይወት ዑደት ምን እንደ ሆነ ታስታውሳለህ? የሕይወት ዑደት አንድ እንስሳ ወይም ሰው ወደ አዋቂነት እንዴት እንደሚለወጥ ያሳየናል።**
- **እስኪ የወፎችን የሕይወት ዑደት እንመልከት።** የአእዋፍን የሕይወት ዑደት ለመግለጽ ስዕሉን ይጠቀሙ - ከእንቁላል ጀምሮ እስከ መፈልፈል፣ እስከ ጫጩትነት፣ እስከ አዋቂ ዶሮ መሆን ድረስ
- ከዚያ በኋላ፣ ልጅዎ እንቆቅልሹን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉት። ከዚያም፣ እንቆቅልሹን እራሱን ችሎ መገጣጠም እንዲችል፣ የተለያዩ ክፍሎቹን እንዲቆራርጥ ይርዱት።



## በግል መማር፥ የእንስሳት መኖሪያን የማዛመድ ጨዋታ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ እንስሳት: የውሃ ውስጥ እንስሳት እና የሳቫና እንስሳት ካርዶች**

- ይህንን ይበሉት፣ **እንስሳት በተለያዩ የመኖሪያ አካባቢዎች ወይም ቦታዎች ይኖራሉ። አንዳንድ እንስሳት በምድር ላይ የሚኖሩ ሲሆን፣ አንዳንድ እንስሳት ደግሞ በውሃ ውስጥ ይኖራሉ። አንዳንድ እንስሳት ደግሞ፣ በሁለቱም ይኖራሉ፣ ለምሳሌ አዞዎች።** የእርሻ እንስሳትን እና የውሃ ውስጥ እንስሳትን ስዕሎች ያሳዩት እና ስለሚኖሩበት ቦታ ይንገሩት።
- የእንስሳትን ስዕሎች በመሬት ላይ የሚኖሩ እና በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት እያልን ለየብቻ እንመድባቸው።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ስዕሎቹን እንዲለዩ ያድርጉት። እርዳታ የሚፈልግ ከሆነ ምንም ችግር የለውም። በደንብ አድናቆት ይስጡት። **በጣም ምርጥ ስራ ነው! በጥንቃቄ እያሰቡ ሲሆን የተቻለህን ያህል ለመስራት እየሞከሩ ነው!**




የሳቫና እንስሳት (FE)


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ማክሰኞ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ቀን 17

## ማንበብና መጻፍ፥ ተራ መመሪያዎች

- ለልጅዎ **እንድትከተላቸው የምፈልጋቸው ተራ መመሪያዎችን እሰጥሀለሁ። በጥንቃቄ አዳምጠኝ** ብለው ይንገሩት።
- ለልጅዎ ተራ ባለ ሁለት ደረጃ መመሪያዎች ይስጡት: እንደ አንበሳ አጓራና ቀጥለህም ጋማህን ነስንስ፣ ልክ እንደ ካንጋሮ ዝለልና ቀጥለህም ፈገግ በል፣ ወዘተ
- ልጅዎ መመሪያዎችን እንዲሰጥዎ ሚናችሁን ተቀያየሩ።

## የጆርናል ሙከራ፥ የወፍ በረር እይታ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከለሮች፣ እርሳስ፣ የወፍ በረር እይታ የጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር እንደ ወፍ መብረር ምን እንደሚመስል እና ስትበሩም ከስር ምን ማየት እንደሚቻል ተነጋገሩ።
- ልጅዎ እንደ ወፍ መብረር ቢችል ምን ማየት እንደሚፈልግ እራሱን ችሎ ስዕል እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- በኋላ ላይም እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **እስኪ እንደ ወፍ መብረር ብትችል ምን ማየት እንደምትፈልግ ንገረኝ።**


ስም፥ ________________

እንደ ወፍ መብረር ብትችል ኖሮ ማየት የሚትፈልገውን አንድ ነገር ስዕል ሳል።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።



ስም፥ _________________


እንደ ወፍ መብረር ብትችል ኖሮ ማየት የምትፈልገውን አንድ ነገር ስዕል ሳል።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ




## STEM: የእንቁራሪት ስብስቦች



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ የእንቁራሪት ስብስቦች፣ ከለሮች፣ ለህጻናት ደህንነቱ የማያሰጋ መቀስ**

- እንዲህ ይበሉት፣ **በዚህ ገጽ ላይ ስንት እንቁራሪቶች እንዳሉ ቁጠር።**
- አሁን፣ እንቁራሪቶቹን ቀለም መቀባት እና ቆርጠህ ማውጣት ትችላለህ። አስፈላጊ ከሆነ፣ ልጅዎን ቆርጦ እንዲያወጣ ሊረዱት ይችላሉ።
- ከዚያ በኋላ፣ ከ 5 የማይበልጡ የተለያዩ የእንቁራሪቶችን ስብስብ እንዲሰራ ልጅዎ ይጠይቁት፣ ለምሳሌ፣ የ 1 እንቁራሪት ስብስብ ስራ፣ የ 2 እንቁራሪቶችን ስብስብ ስራ፣ ወዘተ።

## በግል መማር፥ በእርሻ ማሳ ላይ እንቆቅልሽ።



**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በእርሻ ማሳ ላይ እንቆቅልሽ፣ ከለሮች፣ መቀስ፣** ***በአማራጭነት - ስዕሎቹን ለምሳሌ፣ የእህል ሳጥኖችን ከመቁረጣችሁ በፊት በካርቶኑ ላይ በግሉ ለጥፏቸው***

- እንዲህ ይበሉት፣ **እነዚህን የእርሻ ማሳ ስዕሎች ቀለም መቀባት ትችላለህ። ከዚያም፣ እንቆቅልሹን መስራት እና ቁርጥራጮቹን አንድ ላይ ማያያዝ ትችላለህ።**
- የእንቆቅልሹን ቁርጥራጮች እንዲያወጣ ከማገዝዎ በፊት፣ ልጅዎ ራሱን ችሎ ስዕሎቹን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉት። ከዚያም፣ ራሱን ችሎ እንቆቅልሹን እንዲሰራ ያድርጉት።
- ከዛ በኋላ እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **ስለ እርሻ ማሳው ያስተዋልከውን ነገር ንገረኝ። በእርሻ ማሳ ላይ ሌላ ምን ነገር ልናገኝ እንችላለን?**


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## ማንበብና መጻፍ፥ መቼት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Count the Noisy Birds/ ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር*

- እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **የአንድ ታሪክ መቼት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታስታውሳለህ? መቼት ማለት ታሪኩ የሚከሰትበት ቦታና ጊዜ ማለት ነው። ታሪኮችን የበለጠ ለመረዳት እንድንችል ያግዘናል።**
- *ለ ድምጽ ወፎችን መቁጠር* የሚለውን ያሳዩት። **በስዕሎቹ ውስጥ መቼቱን ማየት እንችላለን። ስለዚህ መቼት ምን ማስተዋል ቻልክ?**
- አዎ፣ መቼቱ ከቤት ውጭ ነው። በተፈጥሮ ውስጥ የሆነ ነው። መቼቱ ዛፍ ነው!




## ያንብቡ፥ ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** *Count the Noisy Birds/ ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር*, **ከቤት እቃዎች ውስጥ 5 ተመሳሳይ ነገሮች፣ ለምሳሌ፣ 5 ማርከሮች**

- ከልጅዎ ጋር ብረው *ሆነው ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር* የሚለውን መጽሃፍ እያነበባችሁ ሳሉ አብራችሁ ቁጠሩ።
- ከዛ በኋላ፣ ገጽ 16-17ን ያሳዩት። **ሰማያዊ ወፎቹን መቁጠር ትችላለህ? ብለው ይጠይቁት። አዎ፣ 4 ናቸው።**
- **እሺ አሁን፣ በ 4 ማርከሮች ስብስብ መስራት ትችላለሁ?** ልጅዎ የሚያደርገውን ሙከራ ማድነቅ እንዳለብዎት አይዘንጉ። **በጣም በርትተህ እየሞከርክ ነው!**





©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ረቡዕ



## እስኪ እንንቀሳቀስ፥ ሳይመን እንዲህ አለ


- እንዲህ ይበሉ፣ **እስኪ ሳይመን ሴይስ/ሳይመን እንዲህ አለ የሚለውን ጨዋታ እንጫወት። እኔ "ሳይመን አለ" እልና አንድ ነገር እንድታደርግ እነግርሃለሁ። "ሳይመን አለ" የሚለውን ከሰማህ፣ እኔ ያልኩትን ማድረግ አለብህ። "ሳይመን አለ" ካላልኩ ደግሞ፣ ምንም ማድረግ የለብህም ማለት ነው።**
- እንደ ውሻ ጩህ፣ ከዛ ደግም ጭራህን አውለብልብ፣ ዝለል እና ከዛ አጨብጭብ፣ ፈገግ በል እና ከዛ እጥፍጥፍ በል፣ ወዘተ ያሉ ባለ 2-ደረጃ መመሪያዎችን ያቅርቡለት።
- ሚና አተቀያየሩ እና ጨዋታውን እሱ ይምራው።

## አንድ ላይ ሆኖ መማር፥ በተፈጥሮ ውስጥ መራመድ


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ማስታወሻ ደብተር ወይም ወረቀት፣ ማርከሮች**

- እንዲህ ይበሉት፣ **ወደ ተፈጥሯዊ አካባቢ የእግር ጉዞ እናድርግ እና ስንት እንስሳትን እንደምናገኝ እንይ እስኪ።**
- በምትጓዙበት ወቅት፣ ልጅዎ የምታዩዋቸውን እንስሳት እንዲመዘግብ ይርዱት፣ ለምሳሌ ወፎች በዛፍ ላይ ወይም ውስጥ ሲበሩ፣ በሳር ውስጥ ነፍሳት ሲንቀሳቀሱ ወዘተ።
- በእግር ጉዞ ከማድረግ ይልቅ፣ በመስኮታችሁ በኩል ወደ ውጭ ማየት ወይም ስልክዎን ወይም ታብሌትዎን በመጠቀም የቨርቹዋል የእንስሳት ማቆያ ቦታን፣ አኳሪየም፣ ወዘተ መጎብኘትም ትችላላችሁ
- የእግር ጉዞውን ካደረጋችሁ በኋላ፣ የምትወዱትን እንስሳ ስዕል አንድ ላይ ሆናችሁ ሳሉ። ወይም ደግሞ፣ በእግር ጉዟችሁ ወቅት ያያችኋቸውን እንስሳት በሙሉ ሳሉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።




©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# ሃሙስ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ቀን 19

## **STEM:** ሞቃት አድርጎ ማቆየት


**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ በረዶ ወይም የቀዘቀዘ ሌላ ነገር፣ 2 ካልሲ፣ ጓንት፣** ***በአማራጭነት - ወረቀት እና ማርከሮች***

- ይህንን ይበሉት፣ **በቀዝቃዛ ቦታዎች የሚኖሩት እንስሳት ሙቀታቸውን ጠብቀቅ እንዲቆዩ የሚያደርጋቸው ብሉበር/ቅባታማ ስብ የተባለ ልዩ ስብ አላቸው።**
- **እስኪ አንድ ሙከራ እንስራ እና ቅባታማ ስብ እንዳለን አስመስለን እናውራ። በመጀመሪያ በረዶውን ንካው። ምን ተሰማህ?**
- **አሁን ደግሞ፣ እስኪ እነዚህ ካልሲዎች የእናንተን ቅባታማ ስብ እንደሆኑ አድርገን እናስብ።** ልጅዎ ሁለቱንም ካልሲዎች በእጁ ላይ እንዲያደርግ ይርዱት። **በረዶውን ስትነካው እጅህን ምን አይነት ስሜት ይሰማሃል? በረዶውን ስትነካ ያልቀዘቀዘህ ለምንድን ነው?**
- *በአማራጭነት - ቅባታማ ስብ በማድረግ እና ሳይኖረው በረዶውን ስለመንካት ያለህን ምልከታ በጽሁፍ ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳል።*

## በግል መማር፥ የወፍ ጎጆ መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥** የወፍ ጎጆ ለመስራት የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ ለምሳሌ፣ ላባ፣ የዛፍ ቅርንጫፎች፣ የመጫወቻ ጭቃ ወይም **[የመጫወቻ ጭቃ አሰራር](#)፣** ክር፣ የጥጥ ኳስ፣ ወይም ሌሎች እንደ እንቁላል አድርገን ልናስባቸው የምንችላቸው ነገሮች

- ከልጅዎ ጋር በመሆን፣ በስልክ ወይም በታብሌት ላይ የወፍ ጎጆ ስዕሎችን ተመልከቱ። ይህንን ይበሉት፣ **ወፎች እንደ ቅርንጫፎች እና ቅጠሎች ያሉ የተለያዩ ነገሮችን በመጠቀም ጎጆ ይሰራሉ። ከዛም እንቁላላቸውን በጎጆው ውስጥ ይጥሉና ጫጩቶቹን ከመፈልፈላቸው በፊት እንቁላላቸውን እንዲሞቅ ያደርጉታል። እነዚህን ነገሮች በመጠቀም የወፍ ጎጆ መስራት ትችላለህ።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ የወፍ ጎጆ እንዲሰራ ያድርጉት።
- ከዛ በኋላ፣ **ስለ ወፍ ጎጆህ ንገረኝ ይበሉት። ለመስራት ምን ምን ተጠቀምክ? እንቁላሉ የት ጋር ያርፋል?**
- *በአማራጭነት - ልጅዎ ሌላ የእንስሳት የመኖሪያ ቦታ ለመስራት የተለያዩ ነገሮችን መጠቀም ይችላል።*



በመጫወቻ ሊጥ የሚደረግ የምግብ ዝግጅት

1 ኩባያ ዱቄት

2 የሻይ ማንኪያ የላመ ክሬም

1/3ኛ ኩባያ ጨው

1 ኩባያ ውሀ

1 የሻይ ማንኪያ የአትክልት ዘይት

የመረጡት አይነት የምግብ ማቅለሚያ

1. ዱቄቱን፣ የላመውን ክሬም እና ጨዉን የምግብ ማብሰያ ድስት ውስጥ ይከተቱ።
2. በምግብ ማብሰያ ድስቱ ውስጥ ውሀና የአትክልት ዘይት ይጨምሩ። ውህዱን በመካከለኛ/አነስተኛ ሙቀት ይቀላቅሉ።
3. ውህዱ መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ማቅለሚያውን ይጨምሩበት።
4. የድስቱ የስረኛው ክፍል ላይ እንዳይይዝ እና እንዳይጋገር ማማሰልዎን ይቀጥሉ።
5. ለጨዋታ ከማዋልዎ በፊት የመጫወቻ ሊጡ እንዲቀዘቅዝ ያድርጉ። ሊጡን አየር በማያስገባ መያዣ ውስጥ ያስቀምጡት።

Playdough Recipe (FE)

©2020. AppleTree Institute. All Rights Reserved.


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።


# ሃሙስ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ቀን 19

## ማንበብና መጻፍ፦ ዋና ገጸ ባህሪ እና መቼት

**የኖላን ሳፋሪ**

FELICIA R. TRUONG, EDD
ሰዐሊ RACHEL ANNE BLIER




**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** *Nolan's Safari/የኖላን ሳፋሪ*

- እንዲህ ብለው ይጠይቁት፣ **የአንድ ታሪክ መቼት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታስታውሳለህ? መቼት ማለት ታሪኩ የሚከሰትበት ቦታና ጊዜ ማለት ነው። ታሪኮችን የበለጠ ለመረዳት እንድንችል ያግዘናል።**
- የኖላን ሳፋሪ የተሰኘውን መጽሃፍ የሽፋን ገጽ እና ሌሎች ገጾችን ያሳዩት። **ስዕሉ መቼቱን ያሳያል። የኖላን ሳፋሪ መቼቱ የት ነው? አዎ፣ ሳቫና ነው።**
- **እዚህ ጋር የሚያዩትን መቼት ይግለጹለት። ማየት የምትችላቸው ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው?**
- **በዚህ መጽሃፍ ውስጥ ዋናኀ ገጸ ባህሪ ማን ነው? መጽሃፉ በብዛት የሚያወራው ስለማን ነው? አዎ፣ ስለ ኖላን። ስለ ኖላን ምን ማስተዋል ትችላለህ?**
- ልጅዎ ድጋፍ ካስፈልገው ምንም ችግር የለውም፣ ገና ለመማር እየሞከሩ ነው፣ በርካታ ማበረታቻዎችን ይስጧቸው። **በጣም እያሰብክ ነው።**

## የጆርናል ሙከራ፦ የእንስሳት የመኖሪያ አካባቢ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፦ ማርከሮች፣ እርሳስ፣ የእንስሳት የመኖሪያ አካባቢ ጆርናል ገጽ**


ስም፦ ________________

ስለምትወዱት የእንስሳ መኖሪያ ጽሁፍ ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።

- ከልጅዎ ጋር ስለ በመሆን ስለተለያዩ የእንስሳት መኖሪያዎች ወይም እንስሳት ስለሚኖሩባቸው ቦታዎች ተነጋገሩ
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ስለሚወደው የእንስሳት መኖሪያ አካባቢ አይነት ስዕል እንዲሰራ እና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- መጨረሻ ላይ እንዲ**እስኪ ስለምትወደው የእንስሳት መኖሪያ አካባቢ አይነት ንገረኝ። ለምንድን ወደድከው?**ህ ብለው ይጠይቁት፣


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ስም፥ ________________

ስለምትወዱት የእንስሳ መኖሪያ ጽሁፍ ጻፉ እንዲሁም ስዕል ሳሉ።



©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ቀን 20

## STEM: ስብስቦችን መስራት

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ከቤት እቃዎች ውስጥ 5 ተመሳሳይ ነገሮች፣ ለምሳሌ፣ 5 ማንኪያ ወይም አሻንጉሊቶች**



- ይህንን ይበሉት፣ **እስኪ በስብስቦች ጨዋታ እንጫወት። ስብስብህን ለመስራት ስንት ነገሮች እንደሚያስፈልጉህ እኔ እነግርሃለሁ።**
- የተለያዩ ትዕዛዛትን ይዘዙት፣ ለምሳሌ፣ የ 3 ማንኪያዎች ስብስብን ስራ፣ የ 5 አሻንጉሊቶችን ስብስብን ስራ፣ ወዘተ።
- ልጅዎ መመሪያዎችን ለእርስዎ መስጠት እንዲችል ሚናዎቻችሁን ተቀያየሩ።

## በግል መማር፥ “የእንስሳት ግዛት: ከሲጥ ሲጥ እስከ ማጓራትን” ተሰናበቱ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፥ ወረቀት፣ ማርከሮች**

- እንዲህ ይበሉት፣ **እስካሁን ድረስ ስለተለያዩ እንስሳት እና የት እንደሚኖሩ እየተማርን ነበር።** ከልጅዎ ጋር ስለተለያዩ እንስሳት እና የት እንደሚኖሩ ከተማሩት ትምህርት የወደዱትን ክፍል አስመልክቶ ተወያዩ። ልጅዎ የመረጠው እንቅስቃሴ ወይም መጽሃፍ ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎ ከዚህ ክፍል ውስጥ ስለወደደው ክፍል ራሱን ችሎ ስዕል እንዲሳል እና እንዲጽፍ ያድርጉት።
- ከዛ በኋላ፣ **ስለ ምንድን ነው የጻፍከው? ይሄን ክፍል የወደድከው ለምንድን ነው?** ብለው ይጠይቁት።


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

# አርብ

PK3 ክፍል 7 ሳምንት 4 ቀን 20

## ማንበብና መጻፍ፡ እስኪ ስለ እንስሳት እናውራ

- እንዲህ ይበሉት፣ **እስካሁን ድረስ ስለተለያዩ እንስሳት እና የት እንደሚኖሩ እየተማርን ነበር። ስለ እንስሳት የተማርከውን አንድ ነገር ልትነግረኝ ትችላለህ?**
- ልጅዎን 2-3 የሚሆኑ ተከታይ ጥያቄዎችን ይጠይቁት ለምሳሌ፣ **ስለ የትኛው እንስሳ የበለጠ መማር ወይም ማወቅ ትፈልጋለህ? ለምን? ወይም የዱር እንስሳ ወይስ የቤት እንስሳ መሆን ትመርጣለህ? ለምን?** እርስ በእርስ ውይይት ማድረግን ተለማመዱ።
- ስለዚህ ርዕስ ማውራት ካልፈለጉ፣ ልጅዎን በምትኩ ስለምን ማውራት እንደሚፈልግ መጠየቅ ይችላሉ።



## ያንብቡ፡ ***Count the Noisy Birds/*** *ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር*

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች፡** *Count the Noisy Birds/ ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር*፣ **ከቤት እቃዎች ውስጥ 5 ተመሳሳይ ነገሮች፣ ለምሳሌ፣ ማርከሮች**

- ከልጅዎ ጋር ብረው *ሆነው ባለ ቅላጼ ወፎችን መቁጠር* የሚለውን መጽሃፍ እያነበባችሁ ሳሉ አብራችሁ ቁጠሩ።
- ከዛ በኋላ፣ ገጽ 12-13ን ያሳዩት። **ቀይ እና ቢጫ ወፎቹን መቁጠር ትችላለህ? ብለው ይጠይቁት። አዎ፣ 5 ናቸው።**
- **እሺ አሁን፣ በ 5 ማርከሮች ስብስብ መስራት ትችላሁ?**



ደራሲና ሰዐሊ Beryl Salinger Schmitt


©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።

ወደ ክፍል 7 እንኳን በደህና መጣችሁ! በክፍል 7 ስር ልጅዎ ስለ እንስሳት እና ስለሚኖሩባቸው የተለያዩ ቦታዎች በተመለከተ ይማራል።



AppleTree

©2021. መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። አፕልትሪ ተቋም። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።